Hima _ Tax Solutions Firm

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 43
ADDIS ABABA 5th July, 2022

## Content

Regulation No. 518/2022
Customs Regulation.................. Page 14310

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፲፰/፪ሺ፲፬
የጉምሩክ ደንብ............................ገጽ ፲፬ሺ፫፻፲

## REGULATION No. 518/2022

## COUNCIL OF MINISTERS CUSTOMS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 180 Sub-Article (1) of the Customs Proclamation No. 859/2014.

## PART ONE

## GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Customs Regulation No. 518/2022".

**2. Definition**

Unless the context otherwise requires in this Regulation:

1/ **"Certificate of Competence"** means a certificate issued by a Commission to for a person who has met the requirement ; human resources and office facilities necessary for a Customs Clearing Agent;

## ደንብ ቁጥር ፭፻፲፰/፪ሺ፲፬

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ አንቀጽ ፩፻፹ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የጉምሩክ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፰/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ **"የብቃት ማረጋገጫ"** ማለት የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለማከናወን የሚያበቁ መስፈርቶችን፣ የሰው ኃይል እና የቢሮ አደረጃጀት አሟልቶ መገኘቱ ለተረጋገጠ ሰው በኮሚሽኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው

ያንዱ ዋጋ Unit Price 236:00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ "የሙያ ማረጋገጫ" ማለት በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለመሰማራት በዚህ ደንብ እና ደንቡን ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ ለተገኘ ሰው በኮሚሽኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፫/ "የጉምሩክ አስተላላፊ" ማለት በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል ተወስኖ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ከማስገባት እና ከሀገር ከማስወጣት ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን የማስፈጸም ተግባር ስለሌላ ሰው ሆኖ የሚያከናውን ሰው ነው፤

፬/ "የዕቃ አስተላላፊነት" የሚለው ሀረግ በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፪ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

፭/ "የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ" ማለት ኤምባሲዎች፣ የቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች፣ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች እና በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የዲፕሎማት ደረጃ ያላቸው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ናቸው፤

፮/ "የከበረ ማዕድን" በማዕድን አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፪ ንዑስ-አንቀጽ (፳፬) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፯/ "የጉምሩክ አማካሪነት የሙያ የምስክር ወረቀት" ማለት ከጉምሩክ ሥራ ጋር በተገናኘ የማማከር ሥራን ለማከናወን የሚያስችል የሙያ ብቃት ላለው ሰው በጉምሩክ ኮሚሽን የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

2/ "Certificate of Professional Qualification" means a certificate issued by the Commission to a person that has fulfilled the criteria laid down in this Regulation and the Directive issued hereunder which will enable it engage in customs clearing business;

3/ "Customs Clearing Agent" means a person who on behalf of another person carry out customs clearance within the Customs territory of Ethiopia in connection with the import and export of goods;

4/ "Freight Forwarding" shall have the meaning ascribed to it under Article 2 Sub-Article (1) of the Freight Forwarding and Ship Agency License Issuance Council of Ministers Regulations No.37/1998;

5/ "Diplomatic Community" means Embassies, Consular Offices, International and Regional Organizations and their officials and employees with diplomatic status;

6/ "Precious Mineral" shall have the meaning ascribed to it under Sub-Article (24) of Article 2 of the Mining Proclamation No. 678/2010 (as amended);

7/ "Customs Advisor Professional Certificate" means a professional certificate issued by the Customs Commission to provide advisory services on matters related to Customs;

Hima _ Tax Solutions Firm

፰/ "ልዩ መብት የተፈቀደለት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ" ማለት በዚህ ደንብ እና ደንቡን መሠረት በማድረግ በሚወጣ መስፈርት መሠረት የተመረጠ የልዩ መብት ተጠቃሚነት መብት የሚያስገኝ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

፱/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፲/ በዚህ ደንብ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በጉምሩክ አዋጅ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት
## ምዕራፍ አንድ
## የመንገደኞች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

### ፫. ስለመንገደኞች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

፩/ ለዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት በሕግ የተሰጠ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ መንገደኛ በአዋጁ በተመለከተው መሠረት በቀይ ወይም በአረንጓዴ ማለፊያ በመጠቀም ስለያዘው ማንኛውም ዕቃ ዲክሌር ማድረግ አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም መንገደኛ የንግድ መጠን ያለው ዕቃ ወይም ገደብ የተደረገበት ዕቃ ወይም የተከለከለ ዕቃ ይዞ የአረንጓዴ ማለፊያ በመጠቀም ማለፍ የለበትም፤

8/ "Authorized Economic Operator" means a person who is selected in accordance with the criteria laid down under this Regulation and Directives issued hereunder and has obtained a certificate which enable him benefit the privileges granted to authorized economic operators;

9/ "Proclamation" means Customs Proclamation No.859/2014 (as amended);

10/ A term used in this Regulation that is defined in the Customs Proclamation shall have the meaning ascribed to it in the Customs Proclamation.

## PART TWO
## CUSTOMS PROCEDURES
## CHAPTER ONE
## PASSENGERS CUSTOMS PROCEDURES

### 3. Customs Procedure Applicable on Passengers

1/ Without prejudice to the rights and privileges granted to diplomatic communities or bodies with special rights, any person who enters in to or departs from Ethiopia shall declare the goods carried by him by using the green or the red channel as provided under the Proclamation;

2/ As provided under Sub-Article (1) of this Article a passenger carrying goods with commercial quantity, restricted or prohibited goods shall not use the green pass channel;

Hima _ Tax Solutions Firm

፫/ በቀይ ማለፊያ ተጠቅሞ ዲክሌር ያደረገ መንገደኛ ሻንጣውን ለጉምሩክ ሹም በማቅረብ ማስፈተሽ ይኖርበታል፤

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) ድንጋጌ ከትራንዚት ክልል በሚወጡ እና ወደ ትራንዚት ክልል በሚገቡ የትራንዚት መንገደኞች ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፤

፭/ በአረንጓዴ ማለፊያ የተጠቀመ መንገደኛ የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ይዟል ብሎ የጠረጠረ የጉምሩክ ሹም መንገደኛውን የመፈተሽ ሥልጣን አለው፤

፮/ በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ ፹፫ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቀይ ማለፊያ ተጠቅሞ ስለያዘው ዕቃ ዲክሌር ያደረገ መንገደኛ ወዲያውኑ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን በወረቀት ፅሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሞልቶ ለጉምሩክ ማቅረብ አለበት፤

፯/ ማንኛውም መንገደኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፭) መሠረት የያዘውን የግል መገልገያ ዕቃ ዲክሌር ያደረገ እና ያስፈተሸ እንደሆነ፤

ሀ) በፍተሻ የተገኘው ወይም ዲክላራሲዮን የቀረበበት ዕቃ የተከለከለ ሆኖ ከተገኘ የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፤

ለ) በፍተሻ የተገኘው ወይም ዲክላራሲዮን የቀረበበት ዕቃ ገደብ የተደረገበት ሆኖ ከተገኘ መንገደኛው ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ፈቃድ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤

3/ A passenger who has declared his goods by using the red channel shall submit his baggage to the customs officer for inspection;

4/ The provisions of Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article shall be applied on transit passengers who enters into and depart from the transit area;

5/ The customs officer has the power to search a passenger who passes through the green channel when he has suspected the passenger of possessing prohibited or restricted goods or goods on which duty and tax should have been paid;

6/ Without prejudice to Article 83 of the Proclamation a passenger who declared his goods by using the red channel shall forthwith submit customs declaration manually or electronically to the customs;

7/ A passenger who declared his goods and inspected in accordance with the provisions of Sub-Article (2) and (5) of this article shall:-

a) without prejudice to the forfeiture of the goods, be criminally liable for the offence committed if goods inspected or declared are identified to be prohibited goods;

b) submit an import permit from the concerned regulatory body for the restricted goods that are found during customs inspection;

ሐ) መንገደኛው ገደብ ለተደረገበት ዕቃ በሕግ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ያላመጣ እንደሆነ ከመቀጫ ነፃ ሆኖ ዕቃው ወደ መጣበት ተመልሶ እንዲወጣ ይደረጋል፤

መ) መንገደኛው ገደብ የተደረገበትን ዕቃ ከሀገር መልሶ የማያስወጣ ከሆነ ዕቃው ተወርሶ እንዲወገድ ይደረጋል፤

ሠ) በፍተሻ የተገኘው ወይም ዲክላራሲዮን የቀረበበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሆኖ ከተገኘ መንገደኛው ቀረጥና ታክሱን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ በተደነገገው መሠረት በቅጣት ወይም ያለቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፤

ረ) በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) የተመለከተው ቢኖርም መንገደኛው የያዘው ዕቃ ዋጋ በመቀጫ ከሚስተናገደው በላይ ሆኖ ከተገኘ ልዩነቱ ይወረሳል፤

፰/ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም በኤክስሬይ ፍተሻ የተገኘ ዕቃ ዲክላራሲዮን እንደቀረበበት ዕቃ አይቆጠርም፡፡

## ፬. የውጭ ምንዛሪና የከበሩ ማዕድናት

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም ገቢ መንገደኛ ወደ ሀገር ውስጥ ይዞ የሚገባው የውጭ ምንዛሪ በብሔራዊ ባንክ ከተፈቀደው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ ለጉምሩክ በጽሑፍ ዲክሌር ማድረግ አለበት፤

c) re-export the restricted goods for which an import permit is not submitted to the customs within the time limit provided by law, without being subject to any penalty;

d) be liable to forfeiture and disposal of the restricted goods for his failure to re-export such goods;

e) pay customs duty and taxes in accordance with Article 5 of this Regulation with or without penalty, as the case may be, on goods declared or detected to be dutiable;

f) notwithstanding the provision of Paragraph (e) of this Sub-Article, be forfeited if the value of the goods exceed the amount that is to be entertained with penalty;

8/ For the purposes of this Regulation, goods identified by X-ray machine shall not be considered as declared goods.

## 4. Foreign Currency and Precious Minerals

1/ Notwithstanding the provisions of Article 3 of this Regulation, any incoming passenger with a possession of a foreign currency in excess of the amount permitted by the National Bank of Ethiopia shall submit a formal customs declaration to the Customs;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ ማንኛውም ወጪ መንገደኛ በሚመለከተው አካል ወይም በሕግ ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ ወይም የከበረ ማዕድን መጠን በላይ ከሀገር ይዞ መውጣት የተከለከለ ነው፤

፫/ ማንኛውም ገቢ መንገደኛ በሚመለከተው አካል ወይም በሕግ ከተፈቀደው የከበረ ማዕድን መጠን በላይ ይዞ ወደ ሀገር መግባት የተከለከለ ነው፤

፬/ ዲክሌር ሳይደረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም ሥልጣን ባለው አካል ከተፈቀደው መጠን በላይ ሆኖ የተገኘ ወይም ወደ ሀገር ሲገባ ከተመዘገበው መጠን በላይ ወደ ውጭ ሀገር ሊወጣ ሲል የተያዘ የውጭ ምንዛሪ እንደማንኛውም የኮንትሮባንድ ዕቃ ተቆጥሮ ይወረሳል፤

፭/ በሕግ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል ከተፈቀደው መጠን በላይ የከበረ ማዕድን ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲያስገባ ወይም ሲያወጣ የተገኘ ሰው በሕግ ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በትርፍነት የተገኘው ማዕድን በጉምሩክ ይወረሳል፡፡

## ፭. የግል መገልገያ ዕቃዎች

፩/ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ማንኛውም መንገደኛ ጠቅላላ ዋጋቸው፣ ዓይነታቸው እና ብዛታቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ ሀገር ሊያስገባ ይችላል፤

2/ An outgoing passenger is not allowed to leave the country with a foreign currency or precious mineral in excess of the amount permitted by the appropriate authority or by law;

3/ Any incoming passenger is not allowed to enter the country with precious minerals in excess of the amount permitted by the appropriate authority or by law;

4/ Any undeclared foreign currency brought into the country or foreign currency in excess of the amount permitted by law or an amount in excess of what was declared by the passenger when entering the country and seized when leaving the country shall be forfeited being considered as contraband good;

5/ A person who is found bringing in or taking away Precious Minerals from Ethiopia shall be legally liable and the Precious minerals shall be forfeited good provided that the amount of such minerals exceed the amount permitted by law or the appropriate authority.

## 5. Personal Effects

1/ A passenger who enters into Ethiopia may import personal effects free of duty and tax the value, type and quantity of which shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry of Finance;

፪/ መንገደኛው ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ዕቃ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከተወሰነው ዋጋ፣ ዓይነት ወይም ብዛት በላይ ያለው ከሆነ በልዩነቱ ላይ ቀረጥና ታክስን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ መቀጮ ይከፍላል፤

፫/ ገቢ መንገደኛው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ በመመሪያ ከተፈቀደለት በላይ ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ በልዩነት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው የግል መገልገያ ዕቃ ውርስ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ መንገደኛው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፤

፬/ በውጭ ሀገር በተለያየ ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ የቆዩ ኢትዮጵያውያን ኑሯቸውን ጠቅልለው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፡-

ሀ) ተሽከርካሪን ሳይጨምር የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱ በውጭ ሀገር ሲጠቀሙባቸው የነበሩ የግልና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፤

ለ) በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው በተጨማሪ አንድ የቤት አውቶሞቢል ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

፭/ ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኙ የኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ሲሰሩ ቆይተው ኑሯቸውን ጠቅልለው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከተዘረዘሩ የግል መገልገያ ዕቃዎች በተጨማሪ አንድ ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር ማስገባት ይችላሉ፤

2/ If the personal effects imported by a passenger exceed the value, type and quantity determined by a Directive of the Ministry of Finance, the passenger shall, without prejudice to the payment of duty and tax, pay a penalty of twice the amount of duties and taxes payable on such goods;

3/ Without prejudice that the personal effects imported by a passenger over two times in excess of the value, type and quantity determined by the Directive shall be forfeited; the passenger shall be criminally liable;

4/ Ethiopian nationals who lived abroad for more than one year for different reasons and returned to Ethiopia on permanent basis may:

a) excluding vehicles, import their personal effects used abroad without paying duties and taxes determined by the Directive of the Ministry of Finance;

b) import one household vehicle by paying duty and tax in addition to personal effects described under Paragraph (a) of this Sub-Article.

5/ Ethiopians who have served in the Ethiopian Government offices abroad for one year or more when they return back to Ethiopia may import one vehicle free of taxes and duties in addition to personal effects to be determined by a Directive issued by the Ministry of Finance ;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) እና (፭) ተፈፃሚ የሚሆነው ተመላሹ ኢትዮጵያዊ በውጭ ሀገር ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ መሆኑን በኖረበት ሀገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ከላከው መሥሪያ ቤት ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፤

፯/ ወጪ መንገደኞች ከሀገር ይዘው እንዲወጡ የሚፈቀድላቸው የዕቃ ዓይነትና መጠን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፰/ በመንገደኞች ሻንጣ ላይ የሚደረገው አካላዊ ፍተሻ የመንገደኞችን እንግልት ማስወገድ በሚያስችል የስጋት ሥራ አመራር መርህ የሚመራ መሆን አለበት፤

፱/ የጉምሩክ ኮሚሽን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር እንዲገቡ እና ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ በገንዘብ ሚኒስቴር የተፈቀዱ እንዲሁም ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

## ፮. <u>ስለመንገደኞች በቅድሚያ የሚሰጥ መረጃ</u>

፩/ ማንኛውም የመንገደኛ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ ስለሚያጓጉዛቸው መንገደኞች ማጓጓዣው ከመድረሱ አራት ሰዓት ቀደም ብሎ በመድረሻ ጣቢያ ለሚገኘው የጉምሩክ ጽሕፈት ቤት የተሟላ መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማስተላለፍ አለበት፤

6/ The provisions of Sub-Article (4) and (5) of this Article shall only apply when the returnee brings an evidence from the Embassy or Consular Office of Ethiopia situated in the country where he used to live or from the public body which assigned him abroad which ascertains that the returnee has stayed abroad for one year or more;

7/ The type, value and quantity of personal effects which outgoing passengers carry at the time of their departure shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry of Finance;

8/ The physical search conducted on passenger baggage shall be governed by strict risk management principles which prevent high inconvenience;

9/ The Customs Commission shall publicize the list of goods that may be imported or exported free of duties and taxes in accordance with the Directive of the Ministry of Finance and goods that are restricted and prohibited.

## 6. <u>Submission of Advanced Passenger Information</u>

1/ Any company that transports passengers to Ethiopia shall provide advance passengers information electronically to the customs office at destination four hours before its arrival;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ጉዞው የሚጠይቀው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ጊዜ ያነሰ ከሆነ ድርጅቱ መረጃውን የሚልከው ማጓጓዣው ጉዞውን ከመጀመሩ አስቀድሞ ይሆናል፤

፫/ ኮሚሽኑ ስለመንገደኞች አስቀድሞ እንዲሰጠው የሚፈልገውን የመረጃ ዓይነት ለአጓጓዦች መግለጽ አለበት፤

፬/ የመንገደኛ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የመንገደኞችን ቅድመ መረጃ ለኮሚሽኑ ያላቀረበ እንደሆነ በእያንዳንዱ ጉዞ የብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር) አስተዳደራዊ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የጉምሩክ ትራንዚት

### ፯. በትራንዚት ስለሚጓጓዙ ዕቃዎች

፩/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አስመዝግቦ ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የትራንዚት ፈቃድ ያገኘ ሰው የትራንዚት ፈቃድ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት አለበት፤

፪/ ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም ከሀገር እንዲወጣ የጉምሩክ ትራንዚት ፈቃድ የተሰጠው ዕቃ ጭነቱ የጉምሩክ መዳረሻ ወይም መውጫ በር እንዲደርስ ኮሚሽኑ በወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ የትራንዚት ሂደቱ መጠናቀቅ አለበት፤

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article where the voyage takes a time lesser than specified under Sub-Article (1) of this Article, the transporter shall provide the information before the commencing the voyage;

3/ The Commission shall notify carriers about the type of information required to be submitted in advance;

4/ A transporter which fails to submit to the Commission an advance passenger information as per Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall be liable to pay an administrative penalty of Birr 100,000 (One Hundred Thousand Birr) for each trip.

## CHAPTER TWO
## CUSTOMS TRANSIT

### 7. Goods on Transit

1/ A person who has filed customs declaration to import goods and has obtained transit permit shall import such goods within one month from the date the transit permit is issued;

2/ A cargo which has obtained transit permit to enter into Ethiopia or to be exported out of Ethiopia shall complete the transit process and arrive at the customs destination or exit port within the time prescribed by the Commission;

Hima _ Tax Solutions Firm

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው በተለያዩ ክፍልፋይ ጭነቶች ከሆነ ለዕቃው የትራንዚት ፈቃድ በተሰጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተጠቃሎ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት አለበት፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፫) የተደነገገው ቢኖርም የትራንዚት ፈቃድ ያገኘ ዕቃ በዚህ ደንብ በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ ሀገር ውስጥ መግባት ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ዕቃው ሀገር ውስጥ እንዲገባ ኮሚሽኑ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል። ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ኮሚሽኑ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፭/ የጉምሩክ አስተላላፊው ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ መድረስ በሚገባው ሰዓት መድረሻ ጣቢያ አለመድረሱን እንዳወቀ ኮሚሽኑ በሚወስነው ጊዜ ይህንኑ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፤

፮/ የዲክላራሲዮን አቅራቢው እና የዕቃ አጓጓዥ ድርጅቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ጉምሩክ መድረሻ ጣቢያ መድረስ በሚገባው ሰዓት ያልደረሰ እንደሆነ ኮሚሽኑ በሚወስነው ጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማሳወቅ አለበት፤

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፭) መሠረት የዲክላራሲዮን አቅራቢው እና የጉምሩክ አስተላላፊው የሚያቀርበው ሪፖርት ዕቃው የዘገየበትን ምክንያት እና የተደረጉ ለውጦች ካሉ ይህንኑ የሚገልጽ መሆን አለበት፤

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article if the goods are to be imported in partial shipments all the goods shall be imported within three months from the date of issuance of the transit permit;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (3) of this Article if it is proved that the cargo was unable to arrive within the time period provided under this Article due to unforeseen circumstances the Commission may grant additional period to enable the cargo enter into the country. The Commission shall develop a procedure for the implementation of this provision;

5/ The Customs Clearing Agent, who is aware of the fact that the goods have not arrived in due time, shall forthwith report to the Commission within the time specified by the Commission;

6/ The Declarant and the transporter shall report to the customs in writing or electronically within the time to be prescribed by the Commission if the goods cannot arrive at the customs destination within the specified time;

7/ The report to be submitted by the Declarant and Customs Clearing Agent in accordance with Sub-Article (5) of this Article shall indicate the reasons for the delay and disclose whether any change is made on the cargo;

Hima _ Tax Solutions Firm

ሐ) መንገደኛው ገደብ ለተደረገበት ዕቃ በሕግ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ያላመጣ እንደሆነ ከመቀጫ ነፃ ሆኖ ዕቃው ወደ መጣበት ተመልሶ እንዲወጣ ይደረጋል፤

መ) መንገደኛው ገደብ የተደረገበትን ዕቃ ከሀገር መልሶ የማያስወጣ ከሆነ ዕቃው ተወርሶ እንዲወገድ ይደረጋል፤

ሠ) በፍተሻ የተገኘው ወይም ዲክላራሲዮን የቀረበበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ የሚከፈልበት ሆኖ ከተገኘ መንገደኛው ቀረጥና ታክሱን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ በተደነገገው መሠረት በቅጣት ወይም ያለቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፤

ረ) በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል ተራ (ሠ) የተመለከተው ቢኖርም መንገደኛው የያዘው ዕቃ ዋጋ በመቀጫ ከሚስተናገደው በላይ ሆኖ ከተገኘ ልዩነቱ ይወረሳል፤

፰/ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም በኤክስሬይ ፍተሻ የተገኘ ዕቃ ዲክላራሲዮን እንደቀረበበት ዕቃ አይቆጠርም፡፡

## ፬. የውጭ ምንዛሪና የከበሩ ማዕድናት

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም ገቢ መንገደኛ ወደ ሀገር ውስጥ ይዞ የሚገባው የውጭ ምንዛሪ በብሔራዊ ባንክ ከተፈቀደው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ ለጉምሩክ በጽሑፍ ዲክሌር ማድረግ አለበት፤

c) re-export the restricted goods for which an import permit is not submitted to the customs within the time limit provided by law, without being subject to any penalty;

d) be liable to forfeiture and disposal of the restricted goods for his failure to re- export such goods;

e) pay customs duty and taxes in accordance with Article 5 of this Regulation with or without penalty, as the case may be, on goods declared or detected to be dutiable;

f) notwithstanding the provision of Paragraph (e) of this Sub-Article, be forfeited if the value of the goods exceed the amount that is to be entertained with penalty;

8/ For the purposes of this Regulation, goods identified by X-ray machine shall not be considered as declared goods.

## 4. Foreign Currency and Precious Minerals

1/ Notwithstanding the provisions of Article 3 of this Regulation, any incoming passenger with a possession of a foreign currency in excess of the amount permitted by the National Bank of Ethiopia shall submit a formal customs declaration to the Customs;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ ማንኛውም ወጪ መንገደኛ በሚመለከተው አካል ወይም በሕግ ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ ወይም የከበረ ማዕድን መጠን በላይ ከሀገር ይዞ መውጣት የተከለከለ ነው፤

፫/ ማንኛውም ገቢ መንገደኛ በሚመለከተው አካል ወይም በሕግ ከተፈቀደው የከበረ ማዕድን መጠን በላይ ይዞ ወደ ሀገር መግባት የተከለከለ ነው፤

፬/ ዲክሌር ሳይደረግ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ወይም ሥልጣን ባለው አካል ከተፈቀደው መጠን በላይ ሆኖ የተገኘ ወይም ወደ ሀገር ሲገባ ከተመዘገበው መጠን በላይ ወደ ውጭ ሀገር ሊወጣ ሲል የተያዘ የውጭ ምንዛሪ እንደማንኛውም የኮንትሮባንድ ዕቃ ተቆጥሮ ይወረሳል፤

፭/ በሕግ ወይም ሥልጣን በተሰጠው አካል ከተፈቀደው መጠን በላይ የከበረ ማዕድን ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲያስገባ ወይም ሲያወጣ የተገኘ ሰው በሕግ ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በትርፍነት የተገኘው ማዕድን በጉምሩክ ይወረሳል፡፡

፭. <u>የግል መገልገያ ዕቃዎች</u>

፩/ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ማንኛውም መንገደኛ ጠቅላላ ዋጋቸው፣ ዓይነታቸው እና ብዛታቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ ሀገር ሊያስገባ ይችላል፤

2/ An outgoing passenger is not allowed to leave the country with a foreign currency or precious mineral in excess of the amount permitted by the appropriate authority or by law;

3/ Any incoming passenger is not allowed to enter the country with precious minerals in excess of the amount permitted by the appropriate authority or by law;

4/ Any undeclared foreign currency brought into the country or foreign currency in excess of the amount permitted by law or an amount in excess of what was declared by the passenger when entering the country and seized when leaving the country shall be forfeited being considered as contraband good;

5/ A person who is found bringing in or taking away Precious Minerals from Ethiopia shall be legally liable and the Precious minerals shall be forfeited good provided that the amount of such minerals exceed the amount permitted by law or the appropriate authority.

5. **<u>Personal Effects</u>**

1/ A passenger who enters into Ethiopia may import personal effects free of duty and tax the value, type and quantity of which shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry of Finance;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ መንገደኛው ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው ዕቃ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከተወሰነው ዋጋ፣ ዓይነት ወይም ብዛት በላይ ያለው ከሆነ በልዩነቱ ላይ ቀረጥና ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ መቀጫ ይከፍላል፤

፫/ ገቢ መንገደኛው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ በመመሪያ ከተፈቀደለት በላይ ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ በልዩነት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባው የግል መገልገያ ዕቃ ውርስ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ መንገደኛው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፤

፬/ በውጭ ሀገር በተለያየ ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ የቆዩ ኢትዮጵያውያን ኑሯቸውን ጠቅልለው ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፡-

ሀ) ተሽከርካሪን ሳይጨምር የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱ በውጭ ሀገር ሲጠቀሙባቸው የነበሩ የግልና የቤት መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፤

ለ) በዚህ ንዑስ-አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው በተጨማሪ አንድ የቤት አውቶሞቢል ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ፡፡

፭/ ከኢትዮጵያ ውጪ በሚገኙ የኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ሲሰሩ ቆይተው ኑሯቸውን ጠቅልለው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ከተዘረዘሩ የግል መገልገያ ዕቃዎች በተጨማሪ አንድ ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር ማስገባት ይችላሉ፤

2/ If the personal effects imported by a passenger exceed the value, type and quantity determined by a Directive of the Ministry of Finance, the passenger shall, without prejudice to the payment of duty and tax, pay a penalty of twice the amount of duties and taxes payable on such goods;

3/ Without prejudice that the personal effects imported by a passenger over two times in excess of the value, type and quantity determined by the Directive shall be forfeited; the passenger shall be criminally liable;

4/ Ethiopian nationals who lived abroad for more than one year for different reasons and returned to Ethiopia on permanent basis may:

a) excluding vehicles, import their personal effects used abroad without paying duties and taxes determined by the Directive of the Ministry of Finance;

b) import one household vehicle by paying duty and tax in addition to personal effects described under Paragraph (a) of this Sub-Article.

5/ Ethiopians who have served in the Ethiopian Government offices abroad for one year or more when they return back to Ethiopia may import one vehicle free of taxes and duties in addition to personal effects to be determined by a Directive issued by the Ministry of Finance ;

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) እና (፭) ተፈፃሚ የሚሆነው ተመላሹ ኢትዮጵያዊ በውጭ ሀገር ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ መሆኑን በኖረበት ሀገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ከላከው መሥሪያ ቤት ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፤

፯/ ወጪ መንገደኞች ከሀገር ይዘው እንዲወጡ የሚፈቀድላቸው የዕቃ ዓይነትና መጠን የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፰/ በመንገደኞች ሻንጣ ላይ የሚደረገው አካላዊ ፍተሻ የመንገደኞችን እንግልት ማስወገድ በሚያስችል የስጋት ሥራ አመራር መርህ የሚመራ መሆን አለበት፤

፱/ የጉምሩክ ኮሚሽን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር እንዲገቡ እና ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ በገንዘብ ሚኒስቴር የተፈቀዱ እንዲሁም ገደብ የተደረገባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ይፋ ማድረግ አለበት።

**፮. <u>ስለመንገደኞች በቅድሚያ የሚሰጥ መረጃ</u>**

፩/ ማንኛውም የመንገደኛ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ ስለሚያጓጉዟቸው መንገደኞች ማጓጓዣው ከመድረሱ አራት ሰዓት ቀደም ብሎ በመድረሻ ጣቢያ ለሚገኘው የጉምሩክ ጽሕፈት ቤት የተሟላ መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማስተላለፍ አለበት፤

6/ The provisions of Sub-Article (4) and (5) of this Article shall only apply when the returnee brings an evidence from the Embassy or Consular Office of Ethiopia situated in the country where he used to live or from the public body which assigned him abroad which ascertains that the returnee has stayed abroad for one year or more;

7/ The type, value and quantity of personal effects which outgoing passengers carry at the time of their departure shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry of Finance;

8/ The physical search conducted on passenger baggage shall be governed by strict risk management principles which prevent high inconvenience;

9/ The Customs Commission shall publicize the list of goods that may be imported or exported free of duties and taxes in accordance with the Directive of the Ministry of Finance and goods that are restricted and prohibited.

**6. <u>Submission of Advanced Passenger Information</u>**

1/ Any company that transports passengers to Ethiopia shall provide advance passengers information electronically to the customs office at destination four hours before its arrival;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ጉዞው የሚጠይቀው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ጊዜ ያነሰ ከሆነ ድርጅቱ፡ መረጃውን የሚልከው ማጓጓዣው ጉዞውን ከመጀመሩ አስቀድሞ ይሆናል፤

፫/ ኮሚሽኑ ስለመንገደኞች አስቀድሞ እንዲሰጠው የሚፈልገውን የመረጃ ዓይነት ለአጓጓዦች መግለጽ አለበት፤

፬/ የመንገደኛ ትራንስፓርት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የመንገደኞችን ቅድመ መረጃ ለኮሚሽኑ ያላቀረበ እንደሆነ በእያንዳንዱ ጉዞ የብር ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር) አስተዳደራዊ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article where the voyage takes a time lesser than specified under Sub-Article (1) of this Article, the transporter shall provide the information before the commencing the voyage;

3/ The Commission shall notify carriers about the type of information required to be submitted in advance;

4/ A transporter which fails to submit to the Commission an advance passenger information as per Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall be liable to pay an administrative penalty of Birr 100,000 (One Hundred Thousand Birr) for each trip.

## ምዕራፍ ሁለት
## የጉምሩክ ትራንዚት

## CHAPTER TWO
## CUSTOMS TRANSIT

### ፯. በትራንዚት ስለሚጓጓዙ ዕቃዎች

፩/ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አስመዝግቦ ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የትራንዚት ፈቃድ ያገኘ ሰው የትራንዚት ፈቃድ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት አለበት፤

፪/ ወደ ሀገር እንዲገባ ወይም ከሀገር እንዲወጣ የጉምሩክ ትራንዚት ፈቃድ የተሰጠው ዕቃ ጭነቱ የጉምሩክ መዳረሻ ወይም መውጫ በር እንዲደርስ ኮሚሽኑ በወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ የትራንዚት ሂደቱ መጠናቀቅ አለበት፤

### 7. Goods on Transit

1/ A person who has filed customs declaration to import goods and has obtained transit permit shall import such goods within one month from the date the transit permit is issued;

2/ A cargo which has obtained transit permit to enter into Ethiopia or to be exported out of Ethiopia shall complete the transit process and arrive at the customs destination or exit port within the time prescribed by the Commission;

Hima _ Tax Solutions Firm

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው በተለያዩ ክፍልፋይ ጭነቶች ከሆነ ለዕቃው የትራንዚት ፈቃድ በተሰጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተጠቃሎ ወደ ሀገር ውስጥ መግባት አለበት፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፫) የተደነገገው ቢኖርም የትራንዚት ፈቃድ ያገኘ ዕቃ በዚህ ደንብ በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ ሀገር ውስጥ መግባት ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ዕቃው ሀገር ውስጥ እንዲገባ ኮሚሽኑ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል። ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ኮሚሽኑ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፭/ የጉምሩክ አስተላላፊው ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ መድረስ በሚገባው ሰዓት መድረሻ ጣቢያ አለመድረሱን እንዳወቀ ኮሚሽኑ በሚወስነው ጊዜ ይህንኑ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፤

፮/ የዲክላራሲዮን አቅራቢው እና የዕቃ አጓጓዥ ድርጅቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ ጉምሩክ መድረሻ ጣቢያ መድረስ በሚገባው ሰዓት ያልደረሰ እንደሆነ ኮሚሽኑ በሚወስነው ጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማሳወቅ አለበት፤

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፭) መሠረት የዲክላራሲዮን አቅራቢው እና የጉምሩክ አስተላላፊው የሚያቀርበው ሪፖርት ዕቃው የዘገየበትን ምክንያት እና የተደረጉ ለውጦች ካሉ ይህንኑ የሚገልጽ መሆን አለበት፤

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article if the goods are to be imported in partial shipments all the goods shall be imported within three months from the date of issuance of the transit permit;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) and (3) of this Article if it is proved that the cargo was unable to arrive within the time period provided under this Article due to unforeseen circumstances the Commission may grant additional period to enable the cargo enter into the country. The Commission shall develop a procedure for the implementation of this provision;

5/ The Customs Clearing Agent, who is aware of the fact that the goods have not arrived in due time, shall forthwith report to the Commission within the time specified by the Commission;

6/ The Declarant and the transporter shall report to the customs in writing or electronically within the time to be prescribed by the Commission if the goods cannot arrive at the customs destination within the specified time;

7/ The report to be submitted by the Declarant and Customs Clearing Agent in accordance with Sub-Article (5) of this Article shall indicate the reasons for the delay and disclose whether any change is made on the cargo;

Hima _ Tax Solutions Firm

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩)፣ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃ ወደጉምሩክ መድረሻ ጣቢያ ያልደረሰ እንደሆነ ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ እንደማይገባ ተቆጥሮ የዕቃ ዲክላራሲዮን ይሰረዛል፤

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፰) ድንጋጌ መሠረት በተሰረዘ ዲክላራሲዮን የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ወይም የተያዘ ዋስትና ተመላሽ ጥያቄ በዲክላራሲዮን አቅራቢው ዲክላራሲዮኑ በተሰረዘ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ለዕቃው ግዥ የዋለው የውጭ ምንዛሪ ለፈቀደው ባንክ መመለሱ ተረጋግጦ ተመላሽ ይደረጋል፤

፲/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መድረስ በሚገባው ሰዓት መውጫ ጣቢያ ባልደረሰ ወይም መውጣት በነበረበት ሰዓት ከሀገር ባልወጣ ተላላፊ የትራንዚት ዕቃ ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

8/ If a cargo does not arrive at the customs destination as provided under Sub-Articles (1), (3) and (4) of this Article the declaration shall be cancelled assuming that the goods will not enter into the country;

9/ The taxes and duties paid or the guarantee submitted in connection with the declaration cancelled in accordance with Sub-Article (8) of this Article shall be returned within one year from the date of cancellation upon submission of evidence showing that the foreign currency used for the purchase of the goods is returned to the approving bank;

10/ The provisions of this Article shall apply on transit goods that did not arrive at customs destination point or depart from the country within the time limit specified.

## ፰. በትራንዚት ላይ እያለ ስለሚጠፋ ጭነት

፩/ በትራንዚት ላይ ያለ ዕቃ በሚጠፋበት ጊዜ አስመጪው እና የጉምሩክ አስተላላፊው ጭነቱ ወይም ዕቃው መጥፋቱን እንዳወቁ ወዲያውኑ በቅርብ ለሚገኝ የሕግ አስከባሪ አካልና ለጉምሩክ መድረሻ ጣቢያ ዝርዝር መረጃ ማቅረብ አለባቸው፤

፪/ የዲክላራሲዮን አቅራቢ እና አጓጓዥ በትራንዚት ላይ እያለ በጠፋ ጭነት ወይም ዕቃ ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ የመክፈል የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው፤

## 8. Goods Lost in Transit

1/ The importer and the Customs Clearing Agent shall forthwith provide detailed information to the nearby law enforcement body and customs station as soon as they know that the cargo or goods in transit are lost;

2/ The Declarant and the carrier shall have joint and several responsibility to pay taxes and duties on goods or cargo that are lost on transit;

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በአጓጓዥ የሚከፈል ቀረጥና ታክስ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም፤

፬/ አስመጪው በጠፋው ጭነት ወይም ዕቃ ላይ አስቀድሞ ቀረጥና ታክስ የከፈለ ወይም ዋስትና ያለው ከሆነ በጠፋው ዕቃ ላይ የከፈለውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል ከአጓጓዡ መጠየቅ ይችላል፡፡

## ፱. በዲክላራሲዮን ሳይመዘገብ ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገባ ተጨማሪ ዕቃ

፩/ አስመጪው በዲክላራሲዮን ሳይመዘገብና መግለጫ ሳይቀርብበት ዲክላራሲዮን ከቀረበበት ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ትርፍ ዕቃ መኖሩን ከመፈተሹ በፊት ለጉምሩክ ካላሳወቀ ወይም ዕቃው ከአስመጪው ትዕዛዝና ፍላጎት ውጪ በላኪው ስህተት ወደ ሀገር ውስጥ የተላከ መሆኑን በማስረጃ ካላረጋገጠ በስተቀር ከሕጋዊ ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ትርፍ ዕቃ በአስመጪው ፍላጎትና ጥያቄ መሠረት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ዕቃ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ተጨማሪ ዕቃ በዲክላራሲዮን ሳይመዘገብ ወደ ሀገር ውስጥ ከሕጋዊ ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ መግባቱን አስመጪው ከፍተሻ በፊት ለጉምሩክ ያስታወቀ እንደሆነ ወይም ዕቃው ወደ ኢትዮጵያ የተላከው ከአስመጪው ትዕዛዝና ፍላጎት ውጪ መሆኑ አስመጪው በሚያቀርበው ማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ በአስመጪው ወጪ ዕቃው ተመልሶ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

3/ Customs duty and taxes to be paid by the carrier in accordance with the provisions of this Article may not preclude criminal liability;

4/ If the importer has paid duties and taxes or provided a guarantee on goods or cargo lost on transit has the right to claim such taxes and duties from the carrier.

## 9. Import of Undeclared Additional Goods

1/ Undeclared goods that are imported along with the legally declared goods shall be considered as imported by the order and interest of the importer unless the importer notifies to the customs before such goods are inspected, or submits evidence which shows that the undeclared goods are imported along with his legally declared goods due to mistakes of the exporter;

2/ The undeclared goods described under Sub-Article (1) of this Article shall be re-exported at the cost of the importer provided that the importer notifies before inspection or proves with evidence that the goods are imported without his order or interest.

**፲. በጎረቤት ሀገር ወደብ ስለሚቆዩ ዕቃዎች**

፩/ በጎረቤት ሀገር ወደብ ከ ፫ ወር በላይ የቆየ ማናቸውም ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወደ ጉምሩክ ክልል ተጓጉዞ በደረቅ ወደብ እንዲቆይ ይደረጋል፤

፪/ የዕቃው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በደረቅ ወደብ እንዲቆይ የተደረገን ዕቃ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በማሟላት እንዲሁም ዕቃውን ለማጓጓዝ የወጣውን ወጪ በመተካት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መረከብ ይችላል፤

፫/ የዕቃው ባለቤት በደረቅ ወደብ የተከማቸን ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያልተረከበ እንደሆነ ዕቃው በሐራጅ እንዲሸጥ ይደረጋል፤

፬/ የገንዘብ ሚኒስቴር ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የሚያግዝ መመሪያ ያወጣል።

## ምዕራፍ ሦስት

## ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የሚፈቀድ ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

**፲፩. ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት**

ኮሚሽኑ፡

፩/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ቀርጾ ተግባራዊ ያደርጋል፤

**10. Goods Not Cleared from Neighbouring Country Ports**

1/ Goods that are not cleared from neighbouring country Port for more than three months from their arrival at such port shall be transported and stored at a dry port in Ethiopia without payment of duties and taxes;

2/ The owner of the goods that are stored in a dry port, in accordance with Sub-Article (1) of this Article, may receive the goods from the dry port upon completing customs formalities and refunding all costs incurred in connection with the transportation of such goods within one month;

3/ If the owner of the goods stored in a dry port is not able to receive the goods within the period specified under Sub-Article (2) of this Article, the goods shall be sold on auction;

4/ The Minister of Finance shall issue Directives for the proper implementation of this Article.

## CHAPTER THREE

## SIMPLIFIED CUSTOMS PROCEDURES FOR AUTHORIZED ECONOMIC OPERATORS

**11. Simplified Procedures**

The Commission shall:

1/ Develop simplified customs procedures for use by Authorized Economic Operators selected in accordance with the Directive issued by the Ministry;

Hima – Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችን በመምረጥ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት ፕሮግራም ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

**፲፪. የመምረጫ መመዘኛዎች**

ማንኛውም ሰው ልዩ መብት የተፈቀደለት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ተብሎ ለመመረጥ:-

፩/ የንግድ እንቅስቃሴውን የሚመራበት ለጉምሩክ ቁጥጥር የሚያመች ዘመናዊ የሪከርድና የመዝገብ አያያዝ ሥርዓት የሚከተል፤

፪/ በጉምሩክ የተረጋገጠ መልካም የሕግ ተገዥነት ሪከርድ ያለው፤

፫/ በውል የሚገባውን ግዴታ የሚወጣ ለመሆኑ በጉምሩክ የሚወሰነውን ዋስትና የሚያቀርብ፤

፬/ በላኪነት፣ በአስመጪነት፣ በአምራችነት፣ በጉምሩክ መጋዘን ባለቤትነት፣ በዕቃ አጓጓዥነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በዕቃ አስተላላፊነት ዘርፍ የተሰማራ፣ መሆን አለበት፡፡

**፲፫. ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የሚውል ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የሚውለው ቀለል ያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚከተሉትን ይጨምራል፤

2/ Register Authorized Economic Operators and provide them with certificates based on the criteria specified under the Directive to be issued by the Ministry hereunder to make them beneficiary of simplified customs procedures.

**12. Criteria for Selection**

A person shall fulfil the following criteria to register as an Authorized Economic Operator:

1/ Have a modern record management and system of registry for the operation of his business that facilitates customs control;

2/ Have positive compliance record confirmed by Customs;

3/ Be capable of providing a guarantee to ensure proper carrying out of his obligations under a contract;

4/ Is engaged in the export, import and manufacturing business, ownership of a Customs Warehouse, serves as a Transporter, Customs Clearing Agent and Freight Forwarding.

**13. Simplified Customs Procedures for Authorized Economic Operators**

1/ Simplified customs Procedures to be provided for Authorized Economic Operators include the following;

ሀ) ዲክላራሲዮን አቅራቢው በቀጣይ የተሟላ ሰነድና ዲክላራሲዮን የሚያቀርብ ስለመሆኑ የጽሑፍ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ በማድረግ ዕቃዎችን ለመለየት በሚያስችል ውስን መረጃ ብቻ የጉምሩክን ፎርማሊቲ በማጠናቀቅ ዕቃዎችን በአፋጣኝ መልቀቅ፤

ለ) ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ አገልግሎት በድርጅቱ መሥሪያ ቦታ እንዲያገኝ ማድረግ፤

ሐ) ዕቃዎችን በተደጋጋሚ የሚልክ ወይም የሚያስመጣ ከሆነ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለሁሉም ወጪና ገቢ ዕቃዎች የተጠቃለለ አንድ ዲክላራሲዮን ብቻ እንዲያቀርብ መፍቀድ፤

መ) የቀረጥና ታክስ ዕዳዎችን በራሱ ወስኖ እንዲያሳውቅ መፍቀድ፤

ሠ)የቅድመ ዕቃ አወጣጥ ሥርዓት የመጠቀም፤

ረ) የቀረጥና ታክስ ክፍያን ዕቃ ለነፃ ዝውውር ከተለቀቀ በኋላ በተራዘመ ጊዜ የመክፈል፤

ሰ) በሁሉም የጉምሩክ አገልግሎቶች ቅድሚያ የማግኘት፡፡

፪/ ኮሚሽኑ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱ ሌሎች የአገልግሎት አሰጣጡን ቀላልና ቀልጣፋ የሚያደርጉ የአሠራር ሥርዓቶችን ሥራ ላይ ማዋል አለበት፤

a) complete simplified customs formalities and release the goods expeditiously by accepting minimum information necessary to identify the goods and by having written undertakings from the Declarant to subsequently complete the formal customs procedure;

b) providing Outdoor Cargo service to the declarant on goods imported and to be exported;

c) providing permission to the declarant who frequently imports or exports goods to submit only one consolidated goods declaration for all imports and exports made in a given period of time;

d) allowing the declarant to assess and declare his duty and tax liabilities by himself;

e) allow release of goods before completion of customs formalities;

f) allow release of goods on deferred payment of taxes and duties;

g) provide priority service in all customs services.

2/ The Commission shall, based on Directives to be issued by the Ministry hereunder, put in place other procedures that facilitate and simplify the rendition of expeditious customs service;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

፫/ ኮሚሽኑ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የሰጣቸውን የምስክር ወረቀት ያግዳል፤ ይሰርዛል፡፡

## ፲፬. ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነት

፩/ በኮሚሽኑ ተመዝግበው የምስክር ወረቀት ለተሰጣቸው ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች አገልግሎት የሚሰጡ ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የተቀላጠፈና የቅድሚያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

፪/ ኮሚሽኑ ልዩ መብት ለተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የታቀፉ ሰዎችን እንዲሁም ለሕግ ተገዢነት የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ሰዎችን ዝርዝር በየወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለጉምሩክ አስተላላፊዎች እና አማካሪዎች

## ምዕራፍ አንድ

## ምልመላ፣ሥልጠና፣ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ መስጠት

## ፲፭. ስለምልመላና ሥልጠና

፩/ ኮሚሽኑ ዕድሜው ከ ፳፩ ዓመት በላይ የሆነ እና በማንኛውም የጉምሩክ ወይም የታክስ ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያልተባለን ማንኛውንም ሰው በመመዝገብ በየጊዜው በሚያወጣው የሥልጠና ፕሮግራም መሠረት

3/ The Commission shall based on the Directive to be issued by the Ministry hereunder suspend; revoke the license of Authorized Economic Operators.

## 14. Responsibilities of Other Concerned Bodies

1/ Government bodies and organizations which provide service to Authorized Economic Operators having certificate of trust and recognition from the Commission shall design and implement a system which enable them to give priority service to Authorized Economic Operators;

2/ The Commission shall frequently provide to the relevant bodies the list of Authorized Economic Operators, which are covered by the program and the list of those whose certificate is revoked.

## PART THREE

## CUSTOMS CLEARING AGENTS AND ADVISORS

## CHAPTER ONE

## RECRUITMENT,TRAINING, ISSUANCE OF CERTIFICATE OF QUALIFICATION AND COMPTENCE

## 15. Recruitment and Training

1/The Commission shall, register persons above 21 years old and not convicted of customs and tax offences to serve as customs clearing agent and provide

የሥልጠና ወጪው በሰልጣኙ እንዲሸፈን በማድረግ የጉምሩክ አስተላላፊነት ስልጠና ይሰጣል ወይም በሶስተኛ ወገን እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ጥፋተኛ የተባለው ሰው ቅጣቱን ከጨረሰ ፭ ዓመት ያለፈው ከሆነ ጥፋተኛ መባሉ በጉምሩክ አስተላላፊነት ከመመልመልና ከመሠልጠን አያግደውም፤

፫/ ለጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠና የሚያበቃው የትምህርት ደረጃና የምልመላ መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፬/ ኮሚሽኑ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎችን ሊሰጥ ይችላል፤

፭/ በማንኛውም የሥነ-ምግባር ጉድለት ያልተሰናበተ፣ በጉምሩክ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ሰጥቶ የለቀቀ የቀድሞ ሠራተኛ ከጉምሩክ ኮሚሽን በለቀቀ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በጉምሩክ አስተላላፊነት እና የጉምሩክ አማካሪነት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችለውን ፈተና ወስዶ ካለፈ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያገኝ ይችላል፤

training or allow third parties to provide training to such recruits at their own cost based on training programs to be developed;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the conviction of the person may not preclude him from recruitment and training as a customs clearing agent where 5 years have lapsed after the completion of the prison sentence;

3/ The educational qualification and criteria of the training shall be determined by a Directive to be issued by the Minister;

4/ The Commission may provide additional training to upgrade professional qualification of customs clearing agent, as the case may be;

5/ Where a former customs officer passes the examination to engage as customs clearing agent and consultant, the Commission may certify him provided that he has served as customs officer for a minimum of Eight years in the Commission and took the examination within three years from the date he has left the Commission and that the officer is not dismissed for serious disciplinary misconducts;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

የሥልጠና ወጪው በሰልጣኙ እንዲሸፈን በማድረግ የጉምሩክ አስተላላፊነት ስልጠና ይሰጣል ወይም በሶስተኛ ወገን እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ጥፋተኛ የተባለው ሰው ቅጣቱን ከጨረሰ ፭ ዓመት ያለፈው ከሆነ ጥፋተኛ መባሉ በጉምሩክ አስተላላፊነት ከመመልመልና ከመሠልጠን አያግደውም፤

፫/ ለጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠና የሚያበቃው የትምህርት ደረጃና የምልመላ መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፬/ ኮሚሽኑ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎችን ሊሰጥ ይችላል፤

፭/ በማንኛውም የሥነ-ምግባር ጉድለት ያልተሰናበተ፣ በጉምሩክ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ሰጥቶ የለቀቀ የቀድሞ ሠራተኛ ከጉምሩክ ኮሚሽን በለቀቀ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በጉምሩክ አስተላላፊነት እና የጉምሩክ አማካሪነት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችለውን ፈተና ወስዶ ካለፈ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊያገኝ ይችላል፤

training or allow third parties to provide training to such recruits at their own cost based on training programs to be developed;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the conviction of the person may not preclude him from recruitment and training as a customs clearing agent where 5 years have lapsed after the completion of the prison sentence;

3/ The educational qualification and criteria of the training shall be determined by a Directive to be issued by the Minister;

4/ The Commission may provide additional training to upgrade professional qualification of customs clearing agent, as the case may be;

5/ Where a former customs officer passes the examination to engage as customs clearing agent and consultant, the Commission may certify him provided that he has served as customs officer for a minimum of Eight years in the Commission and took the examination within three years from the date he has left the Commission and that the officer is not dismissed for serious disciplinary misconducts;

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠውን ሥልጠና ላጠናቀቀ እንዲሁም በንዑስ-አንቀጽ (፭) መሠረት መስፈርቱን አሟልቶ ለተመረጠ ሰው ፈተናውን እና የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው ኮሚሽኑ ይሆናል፡፡

## ፲፮. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

፩/ ኮሚሽኑ የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥልጠናውን በብቃት ላጠናቀቀ እና የሚሰጠውን ፈተና ላለፈ ሠልጣኝ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የምስክር ወረቀቱ ዓይነት፣ ደረጃና ይዘት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፪/ ማንኛውም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በሥራ ላይ ያለ ሰው ኮሚሽኑ በየጊዜው የሚዘጋጀውን የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መውሰድ ይኖርበታል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱን ያከራየ ወይም የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ያልሰራበት ወይም በኮሚሽኑ የሚሰጠውን የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ያልወሰደ እንደሆነ የሙያ ማረጋገጫው የምስክር ወረቀት ይሠረዛል፤

6/ Upon completion of the training provided under Sub-Article (1)and up on fulfilment of the criteria provided under Sub-Article (5) of this Article, the examination and certification of customs clearing agents shall be made by the Commission.

## 16. Certificate of Professional Qualification

1/ The Commission may issue certificate of professional qualification for a trainee who is duly recruited and effectively completed the training of Customs Clearing Agent and passed the examination. The type, contents and the level of the certificate shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry;

2/ Any person who has acquired a certificate of professional qualification shall take professional development courses provided by the Commission that help upgrade his skills;

3/ A person who is provided with a certificate of professional qualification in accordance with Sub-Article (1) of this Article, the certificate of professional qualification shall be cancelled where the licensee leases the license, fails to engage in the Customs Clearing Agent for a year and above or fails to take professional development courses provided by the Commission;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima – Tax Solutions Firm

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት የሙያ ማረጋገጫው የተሰረዘበት ሰው በድጋሚ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው የሚችለው ኮሚሽኑ የሚሰጠውን ሥልጠና እና ፈተና በድጋሚ ወስዶ ሲያልፍ ብቻ ነው፡፡

## ፲፯. የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ስለመስጠት

ኮሚሽኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ለተገኘ ሰው የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ይሠጣል፤

፩/ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው መጠን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸውን ባለሙያዎች ብዛት አሟልቶ የተገኘ፤

፪/ ለሚያከናውነው ሥራ የሚያስፈልገው ቋሚ ቢሮ፣ ስልክ፣ ፋክስ እና ኮምፒውተር ከተዛማጅ የመገናኛ መሳሪያዎች ጋር ያሟላ፤

፫/ ማናቸውንም የሂሳብና የጉምሩክ ሰነዶችን የሚያስቀምጥበት በቂ ስፍራ ያለው፡፡

## ፲፰. የንግድ ሥራ ፈቃድ

፩/ የጉምሩክ አስተላላፊነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ማንኛውም ሰው በጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ለመስራት ከንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው መሆን አለበት፤

4/ A person whose certificate of professional qualification has been cancelled in accordance with Sub-Article (3) of this Article, may regain his certificate only after he re- attended the training provided by the Commission and passed the examination .

## 17. Issuance of Certificate of Competence

The Commission may issue certificate of competence to a person who:-

1/ Engaged professionals with a certificate of professional qualification given in accordance with Article 16 of this Regulation with a number required under the Directive to be issued by the Minister;

2/ Has permanent office with adequate telephone, fax, computer and related communication equipment to carry out the business;

3/ Have sufficient space to keep any correspondence, financial and customs documents.

## 18. Trade License

1/ Any Customs Clearing Agent who has certificate of professional qualification and competence shall have valid trade license from the Ministry of Trade and Regional Integration to carry out customs clearing service;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የራሱን ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ ወይም የሚያስወጣ ሰው ራሱ ወይም የቀጠረው ሠራተኛ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከሆነ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት መፈጸም ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, any importer or exporter may complete customs formalities of his own import or export of goods by himself or by his employee who has the certificate of professional qualification.

**፲፱. ስለ መታወቂያ አሰጣጥ፣ የብቃት ማረጋገጫ አጠቃቀም**

**19. Issuance of Identification Card and Usage of Certificate of Competence**

፩/ ኮሚሽኑ የጉምሩክ አስተላላፊነት መታወቂያ ሊሰጥ የሚችለው በዚህ ደንብ እና ደንቡን መሰረት በማድርግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ ይሆናል፤

1/ The Commission may issue identification card upon ascertaining that a Customs Clearing Agent has fulfilled the requirements under this Regulation and Directive issued by the Minister hereunder;

፪/ ሚኒስቴሩ ስለጉምሩክ አስተላላፊዎች ሥነ ምግባር እንዲሁም የሥራ ብቃት እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታና ስለአጠቃቀሙ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ The Ministry may issue a Directive on code of ethics of Customs Clearing Agents as well as on the use of certificate of professional qualification and competence.

## ምዕራፍ ሁለት
## የሙያ እና ወይም የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

## CHAPTER TWO
## SUSPENSION AND CANCELLATION OF CERTIFICATE OF PROFESSIONAL QUALIFICATION AND/OR COMPETENCE

**፳. የሙያ ብቃት እና/ ወይም የሥራ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድ እና ስለመሰረዝ**

፩/ ኮሚሽኑ ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ፤

**20. Suspension and Cancellation of Certificate of Professional Qualification and/or Competence**

1/ The Commission may suspend or cancel the certificate of professional Qualification or competence issued to a Customs Clearing Agent where the clearing agent is :

Hima _ Tax Solutions Firm

ሀ) ከሙያው ጋር የተዛመዱ ሕጎችን መተላለፉ ከተረጋገጠ፤

ለ) በዚህ ደንብ፣ በአዋጁ ወይም ኮሚሽኑ በሚያስፈፅማቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣለበትን ግዴታ አለመወጣቱ ከተረጋገጠ እንደሁኔታው ፈቃዱን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፤

፪/ የሙያ ብቃት ወይም የሥራ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድና ስለመሰረዝ ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት
## የጉምሩክ አስተላላፊ እና የዕቃ አስተላላፊ ግዴታዎች

### ፳፩. የጉምሩክ አስተላላፊ ግዴታ

ማንኛውም የጉምሩክ አስተላላፊ፡-

፩/ የወከለው ደንበኛ የሰጠውን የውክልና ሥልጣን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ለኮሚሽኑ ወዲያውኑ የማቅረብ፤

፪/ ደንበኛው በሰነዶች ላይ ማንኛውንም ስህተት ወይም ግድፈት በመፈጸም ሕግን አለማክበሩን ካወቀ ሕግ በሚያዘው መሠረት እንዲፈጽም ደንበኛውን የማማከር እና ስህተቱ እንዲታረም የማድረግ፤

፫/ የጉምሩክ ሥራን አስመልክቶ ለደንበኛው የሚሰጠው መረጃ ትክክለኛነት ላይ የማረጋገጥ፤

a) proved to have violated laws related to his profession;

b) proved to have failed to discharge his obligations or responsibilities under this Regulation, the Proclamation and other laws enforced by the Commission;

2/ The Ministry may issue detailed Directives on the suspension and cancellation of certificate of professional qualification or competence.

## CHAPTER THREE
## OBLIGATIONS OF CUSTOMS CLEARING AGENT AND FREIGHT FORWARDER

### 21. Obligations of Customs Clearing Agent

Any Customs Clearing Agent shall:-

1/ Submit to the Commission evidence indicating his authority to act on behalf of his client, when requested by the customs officer;

2/ Promptly advise his client of any of his mistakes or business irregularities in relation to documents and that he has to act in accordance with the law as soon as he is aware of the mistakes of his client;

3/ Ensure as to the legality of information he provides to his client;

፬/ በጉምሩክ በኩል የሚጠየቀውን ቀረጥና ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎችን ወዲያውኑ ለጉምሩክ የመክፈል፣ ቀረጥ እና ታክስ እንዳይሰበሰብ የሚያደርግ ስህተት የፈጸመ እንደሆነ ለቀረጥና ታክስ ክፍያው ከደንበኛው ጋር በአንድነት እና በተናጠል በፍትሐ ብሔር ተጠያቂ የመሆን፤

፭/ የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃዎች በኮሚሽኑ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ተከብረውና ደህንነታቸው ተጠብቆ ወደ ጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ እንዲደርሱ የማድረግ፤

፮/ በማንኛውም የጉምሩክ ጣቢያ ላይ የሚሰራን የጉምሩክ ሹም ወይም ፖሊስ ከማስፈራራት፣ በሀሰት ከመክሰስ፣ ለሕገወጥ ተግባር ከመደለል፣ ውለታዎችን ከመስራት ወይም በጥቅም ትስስር ከመስራት ወይም ጥቅም ከመስጠት ወይም ለመስጠት ከመሞከር የመታቀብ፤

፯/ ሚስጥራዊ የሆኑ የጉምሩክ መረጃዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሕገወጥ መንገድ ለማግኘት ወይም ለማስተላለፍ ከመሞከር የመታቀብ፤

፰/ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ስላስፈጸመባቸው ጉዳዮች፣ ስላከናወናቸው የገንዘብ እንቅስቃሴዎች፣ ስላደረጋቸው የደብዳቤ ልውውጦች እና በአጠቃላይ ከጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ጋር የተዛመዱ የተሟሉ ሰነዶችን የመያዝ፤

4/ Promptly pay duties and taxes, and other fees required by the Customs to be paid on the goods and have joint and several civil liability to duties and taxes with his client if he has committed a fault that rendered the taxes and duties not to be collected;

5/ Ensure safe arrival of the customs transit goods to the customs destination as per the pre-conditions set by the Commission;

6/ Refrain from any act or attempt of threat, false accusation, manipulation, or offering of gifts, promising or allowing unlawful advantages for customs or police officers who are on duty at any customs station;

7/ Refrain from any act or attempt to acquire or transfer directly or indirectly secrete customs information;

8/ Have the obligation to keep all records with respect to cases on which customs formalities are completed and information of all financial transactions, correspondences, and in general all information and complete documents relating to his customs clearing activities;

Hima _ Tax Solutions Firm

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፰) የተመለከቱትን ሰነዶች በማናቸውም ጊዜ በኮሚሽኑ የጉምሩክ ሹም ሲፈለጉ የማስመርመር እና እንደአስፈላጊነቱ የጉምሩክ ሹሙ ቅጂዎችን እንዲወስድ የመፍቀድ፤

፲/ ከሥራው ጋር የተዛመዱ ሰነዶችን ለጉምሩክ ሥራ አፈጻጸም እስከ አምስት ዓመታት ድረስ ይዞ የማቆየት፤

፲፩/ በገቢ ዕቃዎች ከመግቢያ በር እስከ ዕቃው መዳረሻ ድረስ እና ለወጪ ዕቃ ከመነሻ ጣቢያ እስከ መውጫ በር ድረስ ባለው ክልል ብቻ የመስራት፤

ግዴታ አለበት፡፡

## ፳፪. ስለዕቃ አስተላላፊዎች

፩/ የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን የዕቃ አስተላላፊነት ፈቃድ የሚሰጣቸውን እና ፈቃድ የታገደባቸውን ወይም የተሰረዘባቸውን ዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር መረጃ በየጊዜው ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፤

፪/ የዕቃ አስተላላፊው በጉምሩክ ትራንዚት አፈጻጸም ላይ በቀጥታ ተጽዕኖ የሚያመጣ አደጋ ወይም ያልተጠበቀ ሁኔታ ሲከሰት ወዲያወኑ በአቅራቢያው ለሚገኘው የጉምሩክ ጣቢያ ወይም አግባብ ላለው ሌላ የመንግሥት አካል ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

9/ Permit all documents kept in accordance with Sub-Article (8) of this Article to be checked and inspected by customs officer and to take copies of the documents as may be necessary;

10/ Maintain all documents and records related to his activities for a period of five years;

11/ Have an obligation to undertake his business operation of imported goods from gate of entrance to the customs destination of the goods and for export goods from the station of departure to the customs gate of exit.

## 22. Freight Forwarders

1/ The Ethiopian Maritime Authority shall frequently provide the Commission with detailed information as to the issuance, suspension and cancellation of licenses of the Freight Forwarders;

2/ The Freight Forwarder shall forthwith report any risk or unexpected condition that directly affects the customs transit operation to the nearest Customs station or to other concerned government body.

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

## ክፍል አራት
## ስለጉምሩክ መጋዘን
## ምዕራፍ አንድ
## የጉምሩክ መጋዘን ዓይነቶች፣ መስፈርት እና የሚቋቋሙበት ቦታ

**፳፫. በፈቃድ የሚቋቋሙ የመጋዘን ዓይነቶች**

፩/ ኮሚሽኑ በሚሰጠው ፈቃድ የሚቋቋሙ የወልና የግል የጉምሩክ መጋዘኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) የወል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ፣
ለ) የወል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን፣
ሐ) የግል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ መጋዘን፣
መ) የግል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን፣
ሠ) የእርዳታ እቃዎች ማከማቻ ቦንድድ መጋዘን፣
ረ) የቀረጥ ነፃ እቃ መጋዘን፤ እና
ሰ) የቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብር ናቸው፡፡

፪/ የመንግሥት የጉምሩክ መጋዘን የሚቋቋመው በኮሚሽኑ ይሆናል፡፡

፫/ የደረቅ ወደብን በሚመለከት ኮሚሽኑ ፈቃድ የሚሰጠው በደረቅ ወደብ ውስጥ ለሚቋቋሙ የጉምሩክ መጋዘኖች ብቻ ይሆናል፡፡

**፳፬. የወል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የወል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘኖች ሊያሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች**

፩/ በኮንቴይነር ታሽገው ወደ ጉምሩክ መጋዘን ለሚገቡ ዕቃዎች ማከማቻ የሚውል መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፤

ሀ) ከ፵ ቶን በላይ የመመዘን አቅም ያለው የምድር ሚዛን፤

ለ) ከ ፵ ቶን በላይ የመጫን ጉልበት ያለው ሦስትና ከዚያ በላይ መሳሪያ ወይም ጋንትሪ፤

## PART FOUR
## CUSTOMS WAREHOUSE
## CHAPTER ONE
## KINDS OF CUSTOMS WAREHOUSES, CRITERIA AND PLACE OF ESTABLISHMENT

**23. Kinds of Customs Warehouses established by license**

1/ The following public or private customs warehouses may be established by licenses to be issued by the Commission:-

a) Public Temporary Customs Warehous,
b) Public Bonded Customs Warehouse,
c) Private Temporary Customs Warehouse,
d) Private Bonded Customs Warehouse,
e) Relief Goods Bonded Warehouse;
f) Duty Free Store; and
g) Duty Free Shop.

2/ Government customs warehouse shall be established by the Commission.

3/ With respect to dry ports the Commission shall only issue licenses to customs warehouses established within the dry ports.

**24. Criteria for Public Temporary Customs Warehouse or Public Bonded Customs Warehouses**

1/ Warehouses in which goods in a sealed container are stored shall fulfill the following:-

a) a weigh bridge with capacity of 40 tonnes and above;

b) three or more machineries or gantries with a loading capacity of 40 tones and above;

ሐ) ከ ፭ እስከ ፲ ቶን ከብደት ያለው ዕቃ የመጫን ጉልበት ያለው ሶስትና ከዚያ በላይ ፎርክሊፍት፤

መ) በኮንቴነር የመጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነሥርዓት እስኪፈፀምባቸው ድረስ ኮንቴነሮቹ የሚከማቹበት ስፋቱ ከ ፲፭ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ ክፍት ቦታ፤

ሠ) ለዕቃ ፍተሻ የሚያመች በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ ስፋቱ ፫ሺ ካሬ ሜትር ክፍት ስፍራ፤

ረ) ከለላ የተሰራለት ስፋቱ ከ ፪ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ የዕቃ መፈተሻ ቦታ፤

ሰ) ዕቃዎች ተፈትሸው ለነፃ ዝውውር እስኪለቀቁ ድረስ የሚከማቹበት የአንዱ ስፋት ከ ፩ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ ሦስትና ከዚያ በላይ ዝግ መጋዘኖች፤

ሸ) እንደ ዕቃው ባህሪ ለመድሐኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሚበላሽ ዕቃ ማከማቻ ወይም ማቆያ የሚውል የተሟላ መሣሪያና ልዩ እና ዝግ መጋዘን፤

ቀ) የጉምሩክ ማሸጊያ (ሲል)፣ ማሰሪያና መቁረጫ መሣሪያ፤ እና

በ) የዕቃ ማንቀሳቀሻ ጋሪዎች፣ መሰላሎች፣ ሚዛኖች እና መለኪያዎች፡፡

c) three or more forklifts with a loading capacity of 5 to 10 tonnes and above;

d) an open space of above 15,000 metre squares constructed with asphalt or cement concrete used to store staffed container goods until customs procedure is completed;

e) an open space of 3,000 metre squares constructed with asphalt or cement concrete which is suitable for goods inspection;

f) an area of goods inspection with a shaded area of 2,000 meter squares or above constructed with asphalt or cement concrete;

g) three or more closed warehouses with an area of above 1,000 meter squares each used for storing goods until released for free circulation;

h) complete equipment and special and closed warehouse for the storage of goods like food items, medicines, dangerous and perishable goods as their nature requires;

i) equipment used for affixing, strap and cutting customs seal; and

j) wagner, ladders, ground scales and measurement units.

Hima – Tax Solutions Firm

፪/ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ፣የእርሻ መሳሪያዎች እና የተሽከርካሪዎች ማከማቻ መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፤

ሀ) በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ ስፋቱ ከ፩ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ ክፍት ቦታ፤

ለ) ለፍተሻ አመቺ የሆነ የመፈተሻ ጉድጓድና ሊፍት፤

ሐ) የኤሌክትሪክ እና ሌሎች የጥገና አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችሉ መሣሪያዎች ያሉት ጋራዥ፤

መ) በግዢ ወይም በኪራይ የተገኘ የመጎተቻ መሣሪያ፤

፫/ በተሽከርካሪ ላይ እንዳለ የሚፈተሽ ዕቃ የሚከማችበት መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ እና ዕቃ የጫኑ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፋቱ ከ ፪ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ ክፍት ቦታ ያለው፤

ለ) ዕቃ በተሽከርካሪ ላይ እንደተጫነ ለመፈተሽ የሚያስችል በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራና ስፋቱ ከ ፭፻ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ ከለላ የተሰራለት ክፍት ቦታ፤

ሐ) የዕቃ ማንቀሳቀሻ ጋሪዎች፣ መሰላሎች፣ ሚዛኖች እና መለኪያዎች፡፡

፬/ በማናቸውም መጠቅለያ የሚመጣ ዕቃ የሚከማችበት መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) ለምግብ እና ለመድሐኒት ማከማቻነት የሚውሉ የእያንዳንዳቸው ስፋት ከ ፩ሺ፭፻ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ ከሁለት ያላነሱ ዝግ መጋዘኖች፤



2/ Construction machineries, agricultural machineries and vehicles warehouse shall have the following components :-

a) an open space of above 1,000 metre square constructed with asphalt or cement concrete;

b) a garage hole with mobile ladder used for inspecting body of vehicles;

c) garage equipment with necessary electrical and other related maintenance services;

d) a winch leased or purchased.

3/ A warehouse used for the storage of goods inspected as loaded on the truck shall have the following components:

a) an open space with an area of above 2,000 metre squares constructed with asphalt or concrete used for the parking of loaded trucks;

b) shaded open space with an area of above 500 metre squares constructed with asphalt or cement concrete used to inspect loaded trucks;

c) Wagner, ladders, ground scales and measurement units.

4/ warehouses used for the storage of goods in different types of packaging shall have the following components:-

a) not less than two closed warehouses each with an area of 1,500 metre squares used for storing food items and medicines;

Hima – Tax Solutions Firm

ለ) ኬሚካል፣ አደገኛ ዕቃዎች እና ሌሎች ተዛማጅ ዕቃዎች የሚከማቹበት የእያንዳንዳቸው ስፋት ከ ፩ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ ከሁለት ያላነሱ ዝግ ወይም ክፍት መጋዘኖች፤

ሐ) በግዥ ወይም በኪራይ የሚቀርቡ ሶስት ቶን ወይም ከዚያ በላይ ክብደት ያለው ዕቃ ለማንሳት የሚችሉ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ፎርክሊፍቶች ፤

መ) በዕቃ ማስቀመጫ ላይ የሚቀመጡ ዕቃዎች ማኖሪያ ቦታ ወይም በአነስተኛ መጠቅለያ የታሸጉ ዕቃዎች መደርደሪያ እንዲሁም ውድ ለሆኑ እና ልዩ ጥበቃ ለሚሹ ዕቃዎች ማስቀመጫ ካዝና፤ እና

ሠ) የዕቃ ማንቀሳቀሻ ጋሪዎች፣ መሰላሎች፣ ሚዛኖች እና መለኪያዎች፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸውም የወል ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም የወል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘኖች በዚህ አንቀጽ መጋዘኖች እንዲያሟሏቸው ከተጠየቁት በተጨማሪ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

ሀ) ለሚሰጠው የመጋዘን አገልግሎት ባለሙያና የጉልበት ሠራተኞች፤

ለ) ለዕቃዎቹ፣ ለሠራተኞችና ለሌሎች ንብረቶች ደኅንነት ቢያንስ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና መስጫ፣ የውሃ መርጫ ሆዝ እና የመሳሰሉትን የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፤

ሐ) ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና የቢሮ ቁሳቁሶች፤

b) not less than two closed or open warehouses each with an area of above 1,000 metre squares used for storing chemicals, dangerous and other related goods;

c) two or more forklifts that are obtained by lease or purchase and can load or unload three or more tons of goods;

d) pallets used for placing small wrapping or packing items in the shelf and a safe box for keeping precious and susceptible goods safe; and

e) Wagner, ladders, ground scales and measurement units.

5/ Without prejudice to the provisions of Sub-Articles (1), (2), (3) and (4) of this Article, any public temporary customs warehouse or any public bonded warehouse shall in addition to components required under this Article shall have the following components:-

a) professional warehouse employees and workers necessary for the service provided by the warehouse;

b) fire extinguisher, first aid kit, water spraying hoses and similar accident prevention equipment required for the safety of the employees or workers, goods and other properties;

c) offices and office materials necessary for customs activities;

መ) ከተፈቀዱ የጉምሩክ መጋዘኖች በሕግ ተዛውረው የሚመጡ ወይም የተተወ ወይም የተወረሱ ዕቃዎች የሚከማቹባቸው ዝግና ክፍት መጋዘኖች፤

ሠ) ለሠራተኞች እና ለተገልጋዮች የተዘጋጀ ክበብ እና በቂ መፀዳጃ ቦታ፤

ረ) ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚችል ጀኔሬተር እና በቂ የውሃ አቅርቦት፤

ሰ) ለቢሮ አገልግሎት የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራ፤

ሸ) በአግባቡ የተከለለ እና ከሌሎች አገልግሎት መስጫዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ እንዲሁም የደህንነት ካሜራ የተገጠመለት የመጋዘን ሥፍራ፤

ቀ) በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ በኮንክሪት የተሰራ በቂ የተሽከርካሪዎች መተላለፊያ ክፍት ቦታ፤ እና

በ) በመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት፡፡

**፳፭. የግል ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ሊያሟላ የሚገባው መስፈርት**

፩/ በኮንቴይነር እና በመጠቅለያ ታሽገው ወደ ጉምሩክ መጋዘን ለሚገቡ የምርት ግብዓቶች ማከማቻ የሚውል መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ) የግል ወይም በኪራይ የተገኘ ከ ፩ሺ. ካሬ ሜትር በላይ የቦታ ስፋት ያለው ወለሉ በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ መጋዘን፤

d) open and closed warehouses used for the storage of goods transferred from licensed customs warehouses or goods abandoned or forfeited;

e) cafeteria and toilets for workers and customers;

f) a generator capable of providing the necessary service and sufficient water supply;

g) parking lots for office services vehicles;

h) a compound of warehouse with security cameras and proper demarcations and fences that separate the compound from other areas;

i) sufficient area for trafficking trucks in the compound constructed with asphalt or cement concrete; and

j) warehouse management system supported by modern information technology.

**25. Requirements for Establishing Private Bonded Warehouse**

1/ Customs warehouse used for the storage of production inputs with sealed containers and other packing shall have the following components:

a) privately owned or leased warehouse with an area of above 1,000 metre squares and constructed with asphalt or cement concrete;

Hima _ Tax Solutions Firm

ለ) ለዕቃዎች ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፤

ሐ) ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው ዕቃዎች

መ) ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ጀኔሬተር፤

ሠ) ከሌሎች አገልግሎት መስጫዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ እና በአግባቡ የተከለለ የደህንነት ካሜራ የተገጠመለት የመጋዘን ሥፍራ፤

ረ) እንደ ዕቃው ባህሪ ለመድኃኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሚበላሽ ዕቃ ማከማቻ ወይም ማቆያ የሚውል የተሟላ መሣሪያ ያለው ልዩና ዝግ መጋዘን፤

ሰ) የጉምሩክ ማሸጊያ ፣ ማሰሪያና መቁረጫ መሣሪያ፤

ሸ) በመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት፤

ቀ) ዕቃ የጫኑ ተሽከርካሪ ወደ መጋዘኑ ለማስገባት የሚያስችል መተላለፊያ ቦታ ያለው፤

በ) በኮሚሽኑ እና በባለፈቃዱ በጋራ ለመቆለፍ አመቺ የሆነ የመጋዘን በር ያለው፤

ተ) ሦስት ቶን ወይም ከዚያ በላይ ክብደት ያለው ዕቃ ለማንሳት የሚችሉ በግዥ ወይም በኪራይ የተገኙ ሁለት እና ከዚያ በላይ ፎርክሊፍቶች፤ እና

ቸ) ለትራንዚት እና ወደመጋዘኑ በሚገቡ ሌሎች ዕቃዎች ላይ ከሚፈለግ ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ማቅረብ የሚችል፡፡

b) equipment required for the safety of goods and prevention of accidents;

c) office equipped with full furniture and other related materials to facilitate the customs operations;

d) generator required for the business;

e) a compound of warehouse with security cameras and proper demarcations and fences that separate the compound from other areas;

f) complete equipment and special and closed warehouse for the storage of goods like food items, medicines, dangerous and perishable goods as their nature requires;

g) equipment used for affixing, strap and cutting customs seal;

h) warehouse management system supported by modern information technology;

i) sufficient area for trafficking loaded trucks in the compound;

j) a warehouse with a gate lockable jointly with the Commission and the licensee;

k) two or more forklifts that are obtained by lease or purchase and can load three tons or above of goods; and

l) provide a guarantee equal to the taxes and duties payable on goods in transit and entering the warehouse.

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ኮሚሽኑ ሲያምንበት ለሌሎች ዕቃዎች የግል ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

፫/ ለኮንስትራክሽን አገልግሎት የሚውሉ ማሽነሪዎች፣ የሕዝብ ማመላለሻ፣ የደረቅና ፍሳሽ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እና ለእርሻ መሳሪያዎች ማቆያ የሚውል መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) በኮንክሪት ወይም በጠጠር የተሰራ ክፍት መጋዘን፤

ለ) ለዕቃዎች ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፤

ሐ) ለተሽከርካሪ ወይም ማሽነሪ ፍተሻ አመቺ የሆነ የመፈተሻ ቦታና ጉድጓድ፤

መ) ከ ፩ሺ ካሬ ሜትር በላይ የቦታ ስፋትና በኮንክሪት ወይም በአስፋልት የተሰራ የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ ያለው የግል ወይም በኪራይ የተገኘ ክፍት መጋዘን፤

ሠ) ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆነ ቢሮና የቢሮ ዕቃ፤

ረ) በመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት፤ እና

ሰ) በኮሚሽኑ እና በባለፈቃዱ በጋራ ለመቆለፍ አመቺ የሆነ በር ያለው፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, where it is deemed necessary, the Commission may provide private bonded warehouse licence for other goods;

3/ construction machineries, public transport vehicles, dry and liquid cargo trucks and agricultural equipment warehouse shall have the following components :-

a) open warehouse constructed with cement concrete or gravel;

b) equipment required for the safety of goods and prevention of accidents;

c) a garage area and hole suitable for inspecting body of vehicle or machinary;

d) a private owned or leased warehouse with an area of above 1,000 metre squares and constructed with asphalt or cement concrete for parking;

e) office equipped with full furniture and other related materials to facilitate the customs operations;

f) warehouse management system supported by modern information technology; and

g) a warehouse with a gate lockable jointly with the Commission and the licensee.

**፳፮. የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን ሊያሟላ የሚገባው መስፈርት**

በቀረጥ ነፃ መደብር ለሚሸጡ ዕቃዎች ማከማቻ የሚፈቀድ የግል በንድድ መጋዘን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የግል ወይም በኪራይ የተገኘ ከ ፩፻፶ ካሬ ሜትር በላይ የቦታ ስፋት ያለው ዝግ መጋዘን፤

ለ) ለዕቃዎች ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፤

ሐ) ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው ዕቃዎች፤

መ) ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ጀኔሬተር፤

ሠ) ከሌሎች አገልግሎት መስጪያዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ እና የደህንነት ካሜራ የተገጠመለት መጋዘን፤

ረ) እንደ ዕቃው ባህሪ ለዕቃ ማከማቻ ወይም ማቆያ የሚውል የዕቃ መደርደሪያና የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግ መጋዘን፤

ሰ) የጉምሩክ ማሸጊያ፣ ማሰሪያ እና መቁረጫ መሳሪያ፤

ሸ) በመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት፤

ቀ) በኮሚሽኑ እና በባለፈቃዱ በጋራ ለመቆለፍ ምቹ የሆነ፤

በ) ወደመጋዘኑ በሚገባው ዕቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥ እና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና፡፡

**26. Requirements for Establishing Duty Free Store**

Private bonded warehouse licensed for storing goods that are to be sold in a duty free shop shall have the following components:

a) privately owned or leased closed warehouse with an area of above 150 meter squares;

b) fire extinguishing equipment required for the safety of goods and prevention of accidents;

c) office equipped with full furniture and other related materials to facilitate the customs operations;

d) a generator necessary for the work;

e) a compound of warehouse with security cameras and proper demarcations and fences that separate the compound from other areas;

f) depending on the nature of the goods shelves to be used for storing or keeping goods and sufficient closed warehouse;

g) equipment used for affixing, strap and cutting customs seal;

h) warehouse management system supported by modern information technology;

i) conducive to be jointly locked by the Commission and the licensee;

j) a guarantee equal to the taxes and duties payable on goods entering the warehouse.

Hima – Tax Solutions Firm

**፳፯. የእርዳታ ዕቃዎች ማከማቻ ቦንድድ መጋዘን**

ወደ ሀገር የሚገቡ የእርዳታ ዕቃዎች ማከማቻ የሚውል ቦንድድ መጋዘን የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የግል ወይም በኪራይ የተገኘ ወለሉ በአስፋልት ወይም በሲሚንቶ ኮንክሪት የተሰራ መጋዘን፤

ለ) ለዕቃዎች ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፤

ሐ) ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው ዕቃዎች፤

መ) ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ጀኔሬተር፤

ሠ) ከሌሎች አገልግሎት መስጫዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ እና በአግባቡ የተከለለ የደህንነት ካሜራ የተገጠመለት የመጋዘን ሥፍራ፤

ረ) እንደ ዕቃው ባህሪ ለመድኃኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሚበላሽ ዕቃ ማከማቻ ወይም ማቆያ የሚውል የተሟላ መሣሪያ ያለው ልዩና ዝግ መጋዘን፤

ሰ) የጉምሩክ ማሸጊያ ፣ ማሰሪያና መቁረጫ መሣሪያ፤

ሸ) በመረጃ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመጋዘን አስተዳደር ሥርዓት፤

ቀ) ዕቃ የጫኑ ተሽከርካሪ ወደ መጋዘኑ ለማስገባት የሚያስችል መተላለፊያ ቦታ ያለው፤

በ) እንደ አግባብነቱ በኮሚሽኑ የሚራዘም ሆኖ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ መጋዘኑ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፅም፤

ተ) በኮሚሽኑ እና በባለፈቃዱ በጋራ ለመቆለፍ አመቺ የሆነ የመጋዘን በር ያለው፤



**27. Relief Goods Bonded Warehouse**

A bonded warehouse for storing relief goods shall have the following components:

a) privately owned or leased warehouse with asphalt or cement concrete;

b) disaster prevention equipment required for the safety of goods and prevention of accidents;

c) office equipped with full furniture and other related materials to facilitate the customs operations;

d) a generator necessary for the work;

e) a compound of warehouse with security cameras and proper demarcations and fences that separate the compound from other areas;

f) depending on the nature of the good special closed warehouse for storing medicines, foodstuff, dangerous and contaminable goods;

g) equipment used for affixing, strap and cutting customs seal;

h) warehouse management system supported by modern information technology;

i) sufficient area for trafficking loaded trucks to the warehouse;

j) complete customs formalities on goods in the warehouse within six months, which period may be extended by the Commission;

k) a warehouse with a gate conducive to be jointly locked by the Commission and the licensee;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima – Tax Solutions Firm

ቸ) ለትራንዚት እና ወደ መጋዘኑ በሚገቡ ሌሎች ዕቃዎች ላይ ከሚፈለግ ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ማቅረብ የሚችል፤

## ፳፰. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ የሚገኝ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ ፋብሪካ ፈቃድ አሰጣጥ

ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ የሚገኝ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ ፋብሪካ ፈቃድ ለማግኘት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

፩/ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠ የተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፤

፪/ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የግብዓት ምርት ጥመርታ እና የሚያስገባው ግብዓት ዝርዝር ሰነድ፤

፫/ ወደመጋዘኑ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሚሆን የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ባንድ፤

፬/ በአንድ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ የግብዓት እና ያለቀለት ዕቃ መጋዘኖች፤

፭/ ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም እና ቁጥጥር አመቺ የሆነ ከሰራተኞች መግቢያ እና መውጫ የተለየ የዕቃዎች መግቢያ እና መውጫ፤

፮/ ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም እና ቁጥጥር አመቺ የሆነ የተሟላ የቢሮ መገልገያ እና የጉምሩክ የመረጃ ሥርዓት ያለው ቢሮ፤

፯/ ወደ መጋዘን የሚገቡ እና ከመጋዘን የሚወጡ እንዲሁም ከፋብሪካው ወደውጭ የተላኩ ዕቃዎችን መረጃ ለመመዝገብና ለመጠቀም

l) provide a guarantee equal to the taxes and duties payable on goods in transit and entering the warehouse.

## 28. Licencing of Bonded Export Manufacturing Factories Located Outside the Industry Park

Bonded export manufacturing factory located outside the Industry Park shall have the following components to get licence:

1/ Certificate obtained from the Ethiopian Investment Commission or Ministry of Industry indicating that he is beneficiary of the system;

2/ Input output coefficient approved by the relevant organ and lists of inputs;

3/ A bank guarantee or insurance bond for guaranteeing payments of duty and tax on goods entering the warehouse on which duty and tax is not paid;

4/ Inputs warehouse and production warehouse both located in one compound;

5/ Exit and entrance gates of goods separate from exit and entrance gate of employees, which is convenient for customs control;

6/ Office with complete facilities and utilities equipped with customs information system that is convenient for implementing customs procedure and control;

7/ A system of customs registry and record management supported by information technology that clearly indicates goods

Hima – Tax Solutions Firm

የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት፤

፰/ ቅጥር ግቢው በአጥር የተከለለ የደህንነት ካሜራ የተገጠመለት፤እና

፱/ የእሳት አደጋን መከላከል የሚያስችል የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ፡፡

**፳፱. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ የሆነ የቦንድድ የማምረቻ መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥ**

ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ የሆነ የቦንድድ የማምረቻ መጋዘን ፈቃድ ለማግኘት አመልካቹ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

፩/ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠ የቦንድድ የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያለው፤

፪/ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የግብዓት ምርት ጥምርታ እና የሚያስገባውን ግብዓት ዝርዝር በሰነድ የሚያቀርብ፤

፫/ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ መጋዘኑ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል በሚገባው ቀረጥና ታክስ መጠን ለዋስትና የሚሆን የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ የሚያቀርብ፤

፬/ ወደመጋዘን የሚገቡ እና ከመጋዘን የሚወጡ ዕቃዎችን መረጃ ለመመዝገብና ለመጠቀም የሚያስችል በመረጃ ሥርዓት የተደገፈ የጉምሩክ የዕቃ አመዘጋገብ ስርዓት ሥራ ላይ ያዋለ፤

entered into the warehouse for storage and goods withdrawn from the warehouse as well as goods exported from the factory;

8/ A compound fenced and with installed security camera; and

9/ Fire extinguisher for preventing fire accidents.

**29. Licencing of Bonded Manufacturing Warehouse Located Outside Industry Park**

Bonded manufacturing warehouse located outside Industry Park shall fulfil the following components to get licence:-

1/ Certificate obtained from Investment Commission or Ministry of Industry indicating that it is beneficiary of the Bonded manufacturing warehouse system;

2/ An approved document of input output coefficient and lists of inputs to be imported by the importer;

3/ A bank guarantee or insurance bond in an amount equal to taxes and duties on goods to be imported within a year guaranteeing payments of duties and taxes on goods on which duty and tax is not paid;

4/ Introduce Customs goods registration system for registering goods entering and leaving the warehouse which is supported with information system;

፭/ ቅጥር ግቢው በአጥር የተከለለ የድህንነት ካሜራ የተገጠመለት፣

፮/ ከጭነት መኪና ላይ ዕቃ ለመጫን እና ለማውረድ ምቹ መጋዘን ያለው፣ እና

፯/ የእሳት አደጋን መከላከል የሚያስችል የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ፡፡

፴. ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ የሆነ የቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥ

ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ የሆነ የቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን ፈቃድ ለማግኘት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፦

፩/ የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው፣

፪/ ወደሀገር የሚያስገባውን ዕቃ ለወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚዎች የሚሸጥ ከሆነ እንደ አግባብነቱ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን ወይም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠ የአምራች የምስክር ወረቀት እና በሚመለከተው አካል የጸደቀ የግብዓት ምርት ጥመርታ እና ያስገባውን የግብዓት ዝርዝር የሚያሳይ ሰነድ፣

፫/ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ መጋዘኑ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል በሚገባው ቀረጥና ታክስ መጠን ለዋስትና የሚሆን የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ የሚያቀርብ፣

፬/ የግል ወይም በኪራይ የተገኘ ከ፻፶ ካሬ ሜትር በላይ የቦታ ስፋት ያለው ዝግ መጋዘን፣

፭/ ወደመጋዘን የሚገቡ እና ከመጋዘን የሚወጡ ዕቃዎችን መረጃ ለመመዝገብና ለመጠቀም የሚያስችል በመረጃ ሥርዓት የተደገፈ

5/ A compound fenced and installed with a security camera;

6/ A warehouse convenient to load and unload goods from trucks; and

7/ Fire extinguisher for preventing fire accidents.

30. Licencing of Bonded Input Supply Warehouse Located Outside Industry Parks

Bonded input supply warehouse located outside industry parks shall fulfil the following components to get licence:-

1/ Valid business license;

2/ If engaged in supplying its products to beneficiaries of export duty incentive schemes a certificate obtained from the Investment Commission or Ministry of Industry, as appropriate, indicating that he is beneficiary of the schemes, input output coefficient and the list of inputs to be imported all approved by the appropriate organ;

3/ A bank guarantee or insurance bond of an amount sufficient for guaranteeing payments of duties and taxes on imported production inputs within a year on which duty and tax is not paid;

4/ Privately owned or leased closed warehouse with an area of 150 square metres;

5/ Implement a system of customs registry and record management supported by information technology that clearly

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

የጉምሩክ የዕቃ አመዘጋገብ ስርዓት ሥራ ላይ ያዋለ፤

፮/ ለጉምሩክ ኦፊሰር አገልግሎት የሚውል ቢሮና መገልገያ መሣሪያዎች፤

፯/ በመጋዘን ውስጥ እና በቅጥር ግቢው የደህንነት ካሜራ የተገጠመለት ፤

፰/ የጉምሩክ ማሸጊያ፣ ማሰሪያና መቁረጫ መሣሪያ፤

፱/ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ጀኔሬተር፤

፲/ የዕቃ ማንሺያ ፎርክ ሊፍት፣ የዕቃ መደርደሪያ፣ መሰላል የተሟላለት፤

፲፩/ ከጭነት መኪና ላይ ዕቃ ለመጫን እና ለማውረድ ምቹ መጋዘን ያለው፤

፲፪/ የእሳት አደጋን መከላከል የሚያስችል የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያለው፤

፲፫/ ወደ መጋዘኑ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ ከሚፈለግ ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ማቅረብ የሚችል፤እና

፲፬/ በኮሚሽኑ እና በባለፈቃዱ በጋራ ለመቆለፍ አመቺ የሆነ የመጋዘን በር ያለው፡፡

**፴፩. በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚቋቋም ቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ፣ የቦንድድ ፋብሪካ መጋዘን እና የግብዓት አቅርቦት ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥ**

በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚቋቋሙ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ፣ የቦንድድ ፋብሪካ መጋዘን እና የግብዓት አቅርቦት ቦንድድ መጋዘን የሚከተሉትን መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው፡-

፩/ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተሰጠ ሰርተፊኬት፤

indicates goods entered into the warehouse for storage and goods withdrawn from the warehouse;

6/ Fulfil office and office equipment for the customs officer;

7/ Both the warehouse and the fence of the compound shall have installed security camera;

8/ Equipment used for affixing, strap and cutting customs seal;

9/ A generator necessary for the work;

10/ Forklift for lifting goods , shelves with ladder;

11/ A warehouse convenient to load and unload goods from trucks;

12/ Fire extinguisher for preventing fire accidents;

13/ Provide a guarantee equal to the taxes and duties payable on goods entering the warehouse; and

14/ A warehouse gate with conducive to be jointly locked by the Commission and the licensee.

**31. Licencing of Bonded Export Factory, Bonded Factory Warehouse and Bonded Input Supply Warehouse Located Inside Industry Parks**

Bonded Export Factory, Bonded Factory Warehouse and Bonded Input Supply Warehouses located inside Industrial Parks shall fulfil the following components to get licence:-

1/ A certificate issued by the Investment Commission;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የምስክር ወረቀት፤

፫/ በዓመት ውስጥ ወደ መጋዘኑ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በቂ የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና ሰነድ፤

፬/ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የግብዓት ምርት ጥመርታ እና የሚያስገባውን ግብዓት ዝርዝር ለኮሚሽኑ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ፴፪. <u>የጉምሩክ መጋዘን የሚቋቋምባቸው ቦታዎች</u>

፩/ የጉምሩክ መጋዘን የጉምሩክ ጣቢያዎችን በመከተል በሀገሪቷ የአየር፣ የየብስና የውሀ ላይ ማጓጓዣዎች መግቢያና መውጫ በሆኑ የጉምሩክ ወደቦች፤ የመተላለፊያ መንገዶች እንዲሁም በነፃ የንግድ ዞን ወይም በልዩ ኢኮኖሚያዊ ዞን ውስጥ ሊቋቋም ይችላል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ሲያምንበት በሌሎች በማናቸውም ስፍራ የጉምሩክ መጋዘን እንዲቋቋም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ A certificate issued by the concerned regulatory body confirming that it is a beneficiary of export trade incentive schemes;

3/ A bank guarantee or insurance bond of an amount sufficient for guaranteeing payments of duties and taxes on imported production inputs within a year on which duty and tax is not paid;

4/ Input output coefficient approved by the relevant organ and lists of raw inputs to be imported by the importer shall be presented to the Commission.

## 32. <u>Location for the Establishment of Customs Warehouses</u>

1/ Customs warehouses may be established along with customs entry and exit stations for all means of transportation by air, land and water customs ports, transit routes as well as in free trade zones and special economic zones;

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Commission may permit the establishment of customs warehouse in other places.

Hima _ Tax Solutions Firm

**፴፫. ከጉምሩክ ጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ባልወጡ ዕቃዎች ላይ የሚኖር የአስመጪው ኃላፊነት**

፩/ ቀረጥና ታክስ ከተከፈለባቸውና የዕቃ መልቀቂያ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ከጉምሩክ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ላልወጡ ዕቃዎች ሙሉ ኃላፊነት ያለበት የዕቃዎቹ አስመጪ ይሆናል፤

፪/ የጉምሩክ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ባለቤት ኮሚሽኑን በማስፈቀድ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ ከመጋዘን ያልወጡ ዕቃዎችን ወደ ሌላ መጋዘን የማዛወር መብት አለው፤

፫/ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው የዕቃ መልቀቂያ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ ከጉምሩክ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን መውጣት በነበረባቸው ጊዜ ባልወጡ ዕቃዎች ላይ የዕቃዎቹ አስመጪ የመጋዘን ኪራይ በመክፈል ዕቃዎችን ያላስወጣ እንደሆነ የመጋዘኑ ባለቤት ለአስመጪው የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ዕቃዎቹን በሙሉ ወይም በከፊል ሊሸጣቸው ይችላል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት ዕቃዎች ተሸጠው የመጋዘኑ ኪራይ ከተሸፈነ በኋላ የተረፈው ገንዘብ ለዕቃዎቹ አስመጪ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

**33. Obligation of the Importer Who Failed to Clear Goods on time from Temporary Customs Warehouse**

1/ The importer shall be responsible for the goods not cleared out from the temporary customs warehouse after duty and tax is paid and goods released order is issued to him;

2/ The owner of temporary customs warehouse may, with the permission of the Commission, transfer the goods not cleared from the warehouse after completion of customs formalities;

3/ The owner of any temporary customs warehouse may, after giving one month notice, sale , fully or partially, the goods with respect to which the goods importer has failed to clear out from the warehouse by paying the warehouse rent due to him;

4/ After the rent of the warehouse are covered, the remaining amount of proceeds of the goods disposed in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be refunded to the Importer.

Hima _ Tax Solutions Firm

**፴፬. የጉምሩክ መጋዘን የሥራ ቀንና ሰዓት**

፩/ በጉምሩክ መጋዘን ዕቃ ማስገባትና ማስወጣት የሚቻለው የጉምሩክ ጣቢያዎች ወይም ወደቦች ለሥራ ክፍት በሆኑበት የሥራ ቀንና ሰዓት ብቻ ነው፤

፪/ ኮሚሽኑ ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ጊዜ ውጪ ዕቃ ወደ ጉምሩክ መጋዘን እንዲገባ ወይም ከመጋዘን እንዲወጣ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለ መጋዘን ፈቃድ

**፴፭. ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመከልከል**

፩/ ኮሚሽኑ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና ደንቡን መሠረት በማድረግ በሚወጣ መመሪያ የተደነገገውን ለሚያሟላ ማንኛውም አመልካች የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ይሰጣል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ማናቸውም ሰው ፈቃድ ለማግኘት የሚችለው፡-

ሀ) በጽሁፍ ማመልከቻ በማቅረብ፤

ለ) ኮሚሽኑ የሚወስነውን ዋስትና በማስያዝ ይሆናል፡፡

፫/ ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች ከማመልከቻው ጋር፡-

**34. Working Days and Hours of Customs Warehouse**

1/ Goods may enter into or withdrawn from customs warehouses only on the working days and hours of customs stations or ports;

2/ The Commission may, when requested, permit goods to enter into or be withdrawn from the warehouse on other days or hours not covered under Sub-Article (1) of this Article.

## CHAPTER TWO
## WAREHOUSE PERMIT

**35. Granting and Rejecting Warehouse Permit**

1/ The Commission may grant customs warehouse permit for any applicant who fulfils the requirements provided under the provisions of the Proclamation, this Regulation and the Directives to be issued hereunder;

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the applicant for customs warehouse permit shall obtain the permit where the applicant:-

a) submits written application;

b) furnishes guarantee determined by the Commission.

3/ Any applicant who applies for customs warehouse permit shall submit the following together with his written application:

Hima _ Tax Solutions Firm

ሀ) የሚቋቋመውን የጉምሩክ መጋዘን ፕላን፣

ለ) መጋዘኑ ተሠርቶ የተጠናቀቀ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሐ) መጋዘኑ የሚገኝበትን አካባቢና ልዩ ቦታ የሚያሳይ መግለጫ፤ እና

መ) መጋዘኑ የግል ወይም በኪራይ የተገኘ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ ኮሚሽኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ሊከለክል ይችላል፡-

ሀ) የአመልካቹ የሕግ ተገዢነት ሪከርድ መልካም አለመሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ) መጋዘኑ የሚገኝበት ቦታ ለጉምሩክ አገልግሎትና ቁጥጥር አመቺ ካልሆነ፤

ሐ) አመልካቹ በቂ የፋይናንስ አቅም የሌለው እና የተጠየቀውን ዋስትና መጠን ማቅረብ የማይችል ከሆነ፤

መ) የመጋዘን ፈቃድ የተጠየቀባቸው ዕቃዎች ለቁጥጥር አመቺ አለመሆናቸው በኮሚሽኑ ሲታመንበት፡፡

፭/ ኮሚሽኑ የመጋዘን ሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻውን በተቀበለ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የመጋዘን ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል የሳለፈውን ውሳኔ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡



a) the plan of Customs warehouse to be established;

b) document proving the completion of the construction of the warehouse;

c) a statement which indicates the area and specific location of the warehouse; and

d) an evidence showing that the warehouse is owned or leased.

4/ The Commission may refuse to grant customs warehouse permit by the following reasons:

a) where it is established that the compliance records of the applicant is not good;

b) where the location of the warehouse is not convenient for customs service and control;

c) where the applicant is not financially capable and cannot furnish the required amount of guarantee;

d) where the goods for which warehouse permit is requested is believed not to have been convenient for customs control.

5/ The Commission shall notify the applicant, in writing, of its decision of granting or rejecting the application within fifteen days from the receipt of the application.

## ምዕራፍ ሦስት
## የመጋዘን ፈቃድ ስለማደስና ስለመሰረዝ

### ፴፮. የመጋዘን ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትና የሚታደስበት ጊዜ

፩/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፴፯ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃዱ ካልተሰረዘ በስተቀር የተሰጠ የመጋዘን ፈቃድ ለአንድ የበጀት ዓመት የፀና ይሆናል፤

፪/ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሐምሌ ፩ እስከ ሐምሌ ፴ ባለው ጊዜ ውስጥ ተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ተፈጽሞ መታደስ አለበት፤

፫/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ካላሳደሰ ከነሐሴ ፩ እስከ ነሐሴ ፴ ባለው ጊዜ የማደሻውን ፻ ፐርሰንት ቅጣት በመክፈል ያሳድሳል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፫) የተደነገገው ቢኖርም ባለፈቃዱ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የመጋዘን ፈቃዱን ማሳደስ ያልቻለ እንደሆነ አሳማኝ ማስረጃ ሲያቀርብ ፈቃዱ ያለቅጣት በኮሚሽነሩ ወይም እርሱ በሚወክለው ኃላፊ ውሳኔ ሊታደስ ይችላል፤

## CHAPTER THREE
## RENEWAL AND CANCELLATION OF CUSTOMS WAREHOUSE

### 36. Period of Validity and Renewal of Permit

1/ Unless and otherwise the license is cancelled in accordance with reasons provided under the provisions Article 37 of this Regulation, a customs warehouse permit shall be valid for one budget year;

2/ Customs warehouse permit shall be renewed upon payment of the required service fee at the beginning of every Ethiopian budget year from July 1st to July 30th;

3/ The licensee who has not renewed his permit within the time limit specified under Sub-Article (2) of this Article, may renew his permit from August 1st to August 30th Ethiopian budget year with the payment of a penalty of 100 percent of the service fee;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (2) and (3) of this Article, where the warehouse licensee establishes that he was not able to renew his permit due to force majeure, the permit may be renewed upon the decision of the Commissioner or his representative without penalty;

Hima _ Tax Solutions Firm

፭/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ፈቃዱን እንዳያድስ ምክንያት የሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፩ሺ፯፻፺፪ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

**፴፯. የተሰጠ የመጋዘን ፈቃድ የሚሰረዝባቸው ምክንያቶች**

፩/ ኮሚሽኑ በዚህ ደንብ መሠረት የሰጠውን የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ያለቅድመ ሁኔታ ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ ያልተመዘገበ ወይም ፈቃድ ያልተሰጠው ዕቃ እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ከተደረገ፤

ለ) የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከመጋዘን እንዲወጣ ከተደረገ፤

ሐ) ወደተፈቀደው መጋዘን ስለገቡ ዕቃዎች የሚገልጹ ሠነዶች ከተሰረዙ ወይም ከተደለዙ፤

መ) ወደተፈቀደው መጋዘን ያልገባን ዕቃ እንደገባ አስመስሎ የተዘጋጀ የሀሰት ማስረጃ ከቀረበ፣ ወይም የማጭበርበር ተግባር ከተፈፀመ፤

ሠ) ወደ መጋዘኑ በገቡ ዕቃዎች ላይ ስርቆት የተፈፀመ እና የመጋዘኑ ባለቤት በድርጊቱ የተባበረ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ረ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፮ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ሳይታደስ የቀረ እንደሆነ፤

5/ for the purposes of this Article "force majeure" shall mean conditions provided under Article 1792 of the Civil Code of Ethiopia which prevents the owner of the permit from renewing his permit within the time specified by law.

**37. Reasons for Cancellation of Customs Warehouse License**

1/ The Commission may unconditionally revoke the warehouse permit issued under this Regulation where the licensee:-

a) allows unauthorized or unregistered goods to enter into or withdrawn from the warehouse;

b) withdraws goods upon which the customs formality is not accomplished,

c) cancels or deletes documents describing goods that have entered into the permitted warehouse;

d) provides false evidences or commits fraudulent acts pretending the entry of goods into the permitted warehouse that are not actually entered;

e) goods entered into the warehouse are stolen and it is proved that the licensee has cooperated with such act;

f) failed to renew his permit in accordance with Article 36 of this Regulation;

Hima _ Tax Solutions Firm

ሰ) ባለፈቃዱ የመጋዘን ፈቃዱን ከወሰደበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምንም አይነት ዕቃ ወደተፈቀደለት መጋዘን ያላስገባ እንደሆነ፡፡

፪/ ከዚህ በታች የተገለጹት ሲፈፀሙ ኮሚሽኑ በቅድሚያ የአሥር ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመጋዘን ፈቃድ ይሰርዛል፡-

ሀ) በሕግ ወይም ኮሚሽኑ ባወጣቸው መመሪያዎች ውስጥ የተደነገጉትን የሚጥስ ተግባር ከተፈፀመ፤

ለ) የኮሚሽኑ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የዕለት ተግባራቸውን እንዲፈጽሙ ትብብር ካልተደረገ፤

ሐ) በጥንቃቄ ጉድለት በዕቃዎች ላይ ጉዳት ከደረሰ፤

መ) የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመባቸው ወይም በባለቤቱ የተተወ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገዱ፣ የተወረሱ እና የመሳሰሉት ዕቃዎች ወደ ጉምሩክ የመንግስት መጋዘን በወቅቱ ካልተላለፉ፤ወይም

ሠ) ባለፈቃዱ የተፈቀዱ ናሙናዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የተሰጡ ናሙናዎችን ተከታትሎ ካላስመለሰ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ቢኖርም በማስጠንቀቂያ ጊዜ ገደቡ ውስጥ እንዲስተካከሉ በኮሚሽኑ በጽሑፍ ለባለፈቃዱ የተገለጹ ጉዳዮች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መስተካከላቸው ሲረጋገጥ የመጋዘን ፈቃድ ስረዛው ቀሪ ሊደረግ ይችላል፤

g) the licensee has not stored any good in the warehouse within one year from the issuance of the license.

2/ The Commission may revoke Customs Warehouse permit for any of the following reasons by giving ten days prior notice to the licensee where the licensee:

a) fails to comply with the conditions specified by law or Directives issued by the Commission;

b) is not cooperative to customs officials and employees who are on duty;

c) causes damage on goods due to mishandling or negligence;

d) failed to transfer goods that are abandoned or attached by court order, forfeited, and goods upon which customs formalities are not accomplished to the government warehouse on due time; or

e) fails to provide required samples or collect samples which are provided earlier or report in due time.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the Commission may not revoke the permit; provided that the defects notified to the licensee by the Commission are correctly and completely rectified within the time specified in the notification of the Commission;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

፬/ በዚህ አንቀጽ በተመለከቱት ምክንያቶች ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው በድጋሚ የመጋዘን ፈቃድ የሚያገኘው ፈቃዱ ከተሰረዘበት ከአንድ ዓመት በኋላ መመዘኛውን አሟልቶ ሲገኝ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር
## ምዕራፍ አንድ
## የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ስለማቋቋም

### ፴፰. የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ

፩/ ኮሚሽኑ በዚህ የደንቡ ክፍል የተመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ ማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ፈቃዱ እንዲሰጠው ለኮሚሽኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

### ፴፱. የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ከማመልከቻው ጋር አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡-

፩/ የአስመጪነት ፈቃድ፤

፪/ የካፒታል መጠኑ ፲ ሚሊዮን ብር (አስር ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በላይ የሆነ የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ፤

4/ A person whose permit has been cancelled with reasons provided under this Article may regain his warehouse permit after one year from the date of cancelation upon fulfilling the requirements.

## PART FIVE
## DUTY FREE SHOP
## CHAPTER ONE
## ESTABLISHMENT OF DUTY FREE SHOPS

### 38. Duty Free Shop Permit

1/ The Commission may grant duty free shop permit for any Ethiopian national who fulfils the conditions provided under this Part of the Regulation;

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article any person applying for a duty-free shop permit shall submit his application to the Commission.

### 39. Preconditions for Obtaining Duty Free Shop Permit

Any person applying for a duty free shop permit shall submit the following documents with his application:-

1/ Import license;

2/ Retailer license with Birr 10,000,000.00 (Ten Million Ethiopian Birr) or above capital;

፫/ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ የወጣበት የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን፡፡

3/ Duty free store for which a customs warehouse permit is granted for.

## ፵. የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ

የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት ማንኛውም ሰው በማመልከቻው ውስጥ የሚከተሉትን መግለጽ እና ማስረጃ ማያያዝ ይኖርበታል፡-

፩/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫው መደብር ባለቤት ሙሉ ስምና አድራሻ፤

፪/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫው መደብር እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን አድራሻ፤

፫/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫውን መደብር የሚሸጣቸውን ዕቃዎች ዓይነት፤

፬/ ዓመታዊ የአቅርቦት መጠን ግምት፤

፭/ የቀረጥ ነፃ መደብሩ እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን የግል ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታና ፕላን፤

፮/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እና/ወይም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን የኪራይ ከሆነ ከአከራዩ ጋር የተደረገ የኪራይ ውል ስምምነት፤

፯/ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ በውጭ ምንዛሪ የሚሰራ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ፤

## 40. Application Lodged to Obtain Duty Free Shop Permit

Any person applying for a Duty-Free Shop permit shall submit his application supported by the following documents and statements:

1/ Full name and address of the owner of the duty-free shop;

2/ Physical address of the duty-free shop and duty-free store;

3/ Type of goods to be sold at the duty-free shop;

4/ The annual quantity of supply;

5/ Title deed and plan of the duty free shop and duty free store where the shop and store is owned by the licensee;

6/ A copy of the rental agreement for the duty free-shop and/or the Duty Free Store where the shop and the store are obtained by lease;

7/ A cash register machine which is programed to operate in foreign currency approved and registered by the concerned organ,

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

## ፵፩. የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ስለሚቋቋምበት ቦታ

፩/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ማቋቋም የሚቻለው፡-

ሀ) በዓለም አቀፍ ኤርፖርቶች፣

ለ) በተፈቀዱ የጉምሩክ መውጫና መግቢያ በሮች፣

ሐ) በአፍሪካ ህብረት ጽሕፈት ቤት፣

መ) በአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት፣

ሠ) አራት ኮከብ እና ከዚያ በላይ ደረጃ ባላቸው ሆቴሎች፣ እና

ረ) ሚኒስትሩ በልዩ ሁኔታ በሚወስናቸው ሌሎች ቦታዎች ነው፡፡

፪/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እንዲቋቋምባቸው የሚመረጡ ሆቴሎችና የገበያ ማዕከላት እንዲሁም በልዩ ሁኔታ የሚፈቀዱ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮች በተጨማሪነት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብርን ፈቃድ ስለማደስ፣ ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

## ፵፪. ፈቃድ ስለማደስ

፩/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለፈቃድ ሀገራዊ የንግድ ስራ ማሳደሻ ጊዜ ባበቃ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኮሚሽኑ የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ በመክፈል የቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብር ፈቃዱን ማሳደስ ይኖርበታል፤

## 41. Places Where Duty Free Shops shall be Established

1/ Duty Free Shops shall be established only in the following places:-.

a) at international air ports;

b) at customs entrance and exit points;

c) in the office of African Union;

d) in the office of African Economic Commission;

e) in hotels with four star and above; and

f) other places to be determined by the Minister in special cases.

2/ Additional pre-conditions which shall be fulfilled by Hotels selected for the establishment of duty-free shops and other places where duty free shops are to be established by special permission shall be described by a Directive to be issued by the Ministry.

## CHAPTER TWO

## RENEWAL, SUSPENSION AND CANCELLATION OF DUTY FREE SHOP PERMIT

## 42. Renewal of Permit

1/The owner of a duty free shop shall renew his permit within one month from the last date of national annual business license renewal by making payments of renewal fee to the Commission;

፪/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተገለፀው የጊዜ ገደብ ማሳደስ ካልቻለ በተጨማሪ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማደሻውን ፻ ፐርሰንት መቀጫ በመክፈል ማሳደስ ይችላል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ባለፈቃዱ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ፈቃዱን ማሳደስ ያልቻለ ለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ሲቀርብ ያለቅጣት በኮሚሽነሩ ወይም ኮሚሽነሩ በሚወክለው ኃላፊ ውሳኔ ሊታደስ ይችላል፤

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ፈቃዱን እንዳያድስ ምክንያት የሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፩ሺ፯፻፺፪ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## ፵፫. ፈቃድ ለማሳደስ ሊሟሉ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

፩/ ባለፈቃዱ የተሰጠውን የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ ለማሳደስ የሚከተሉትን ሰነዶች ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የቀዳሚ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት፤

ለ) የታደሰ የአስመጪነት እና የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ፤

ሐ) የታደሰ የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና፤እና

መ) የታደሰ የቀረጥ ነጻ መጋዘን ፈቃድ፡፡

2/Where the owner of the permit fails to renew his permit with in the time limit provided under Sub-Article (1) of this Article he may renew the permit by paying a penalty of 100 percent of the renewal fee within one month additional time;

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article, the owner of the permit who has established force majeure for the failure of renewal of the permit with in the time specified under the provisions of this Article may renew his permit without penalty by the decision of the Commissioner or his representative;

4/ For purposes of this Article ''force majeure'' shall mean conditions provided under Article 1792 of the Civil Code of Ethiopia which prevents the person from renewing his permit within the time specified by law.

## 43. Preconditions to be fulfilled for the Renewal of Permit

1/ The owner of the permit shall submit the following documents to the Commission to renew his duty free shop permit:-

a) financial report of the preceding year;

b) renewed import and retail license;

c) renewed bank guarantee or insurance bond; and

d) renewed duty free store permit.

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ፈቃዱን ያድሳል፡፡

**፵፬. ፈቃድ ስለማገድና ስለመሰረዝ**

፩/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ እስኪታረም ድረስ ድርጅቱ ወደተፈቀደለት የቀረጥ ነፃ መጋዘን ዕቃ እንዳያስገባ እና ወደቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር የገቡ ዕቃዎች እንዳይሸጡ ኮሚሽኑ ፈቃዱን አግዶ ሊያቆይ ይችላል፡-

ሀ) ወቅታዊ የሽያጭና የዕቃ ክምችት ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

ለ) የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ያልገዛ ወይም ያልተጠቀመ እንደሆነ፤

ሐ) ደረሰኝ ሳያሳትም ሥራ የጀመረ እንደሆነ፤

መ) የንግድና የሒሳብ መዝገብ ያልያዘ እንደሆነ፤

ሠ) የመረጃና የሪከርድ ሥርዓቱ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እንደሆነ፤እና

ረ) የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃድ ያላሳደሰ እንደሆነ፡፡

፪/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት የሚከተሉትን ጥፋቶች የፈፀመ እንደሆነ ኮሚሽኑ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ፈቃዱን ያለቅድመ ሁኔታ ይሰርዛል፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተጠቀሱት ምክንያቶች ፈቃዱ ከታገደበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥፋቱን ያላረመ እንደሆነ፤

2/ The Commission shall renew the duty free shop permit by ascertaining the fulfilment of the conditions provided under Sub-Article (1) of this Article.

**44. Suspension and Cancellation of Permit**

1/ The Commission may suspend the permit and prevent goods from entering and leaving the duty free shops until the owner of the permit takes remedial action on the following defaults:

a) failure to produce timely sales and stock report;

b) failure to purchase or use cash register machine;

c) operates business without getting receipts printed;

d) failure to keep commercial and financial books of record;

e) failure to support his system of record and documentation by technology; and

f) failure to renew his Duty Free Store permit.

2/ The Commission may unconditionally cancel the duty free shop permit where the owner of the permit:

a) fails to take remedial action on reasons specified under Sub-Article (1) of this Article within three months from the date of suspension;

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

ለ) ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ የመግዛት መብት ለሌላቸው ሰዎች ዕቃ መሸጡ የተረጋገጠ እንደሆነ፤

ሐ) በኢትዮጵያ ብር ዕቃ የሸጠ እንደሆነ፤

መ) ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከሽያጭ ያገኘውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ የማያደርግ ከሆነ፤

ሠ) መክፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በወቅቱ የማይከፍል ከሆነ፤

ረ) ያለደረሰኝ ሽያጭ ያከናወነ እንደሆነ፤እና

ሰ) በተፈቀደለት የቀረጥ ነፃ መሸጫ መደብር ሽፋን ማንኛውንም የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፡፡

b) is proved to have sold goods for persons who have no rights to purchase goods from duty free shops;

c) is found to have sold goods in Ethiopian Birr;

d) fails to deposit the foreign currency from the proceeds of his sale in accordance with Directives to be issued by the National Bank of Ethiopia;

e) fails to timely pay Customs Duty and taxes due to him;

f) is found to have performed sales transaction without receipt; and

g) commits any customs fraudulent acts under the cover of the duty free shop.

## ምዕራፍ ሦስት
## የተጠቃሚዎችና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤቶች መብትና ግዴታ

### ፵፭. ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ የመግዛት መብት

፩/ ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ የመግዛት መብት ያላቸው የሚከተሉት ሰዎች ብቻ ናቸው፡-

ሀ) ማንኛውም ወደ ሀገር የሚገባ መንገደኛ፤

ለ) የትራንዚት መንገደኛ፤

ሐ) ማንኛውም ከሀገር የሚወጣ መንገደኛ፤

መ) ኤምባሲዎች፣ የቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች፣ ዓለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ ድርጅቶች፤እና

## CHAPTER THREE
## RIGHTS AND DUTIES OF DUTY FREE SHOP OWNERS AND BENEFICIARIES

### 45. Right to Buy Goods from Duty Free Shops

1/ Only the following Persons have the right to buy goods from duty free shops;

a) any incoming passenger to the country;

b) transit passengers;

c) any outgoing passengers from the country;

d) Embassies, Consular Offices, International or Regional Organizations; and

Hima _ Tax Solutions Firm

ሠ) ዲፕሎማቶች፣ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣ በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ሠራተኞች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) የተጠቀሱት ተጠቃሚዎች የቀረጥ ነፃ ዕቃ መግዛት የሚችሉት በዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎችና በጉምሩክ መውጫና መግቢያ በሮች፣ ከተቋቋሙ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮች ነው፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (መ) እና (ሠ) የተጠቀሱት ተጠቃሚዎች ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ መግዛት የሚችሉት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እና ኮሚሽኑ በልዩ ሁኔታ በሰጠው ፈቃድ ከተቋቋሙ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮች ብቻ ይሆናል፤

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፫) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም መንገደኛ ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ መግዛት የሚችለው የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያን ከማለፉ በፊት ብቻ ነው፤

፭/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የማናቸውም አየር መንገድ እና የባቡር ትራንስፖርት ኩባንያ ሠራተኞች ወይም በሥራቸው ምክንያት የበረራ ወይም የባቡር ትራንስፖርት አባል ሆነው ለሥራ ከተጓዙ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ እንደ ገቢ መንገደኛ አይቆጠሩም፡፡

e) Diplomats, Diplomatic Missionaries and employees of International or Regional Organizations who have duty free privileges.

2/ Beneficiaries described under the provisions of Paragraph (a), (b) and (c) of Sub-Article (1) of this Article may purchase duty free goods from international air ports at customs entrance and exit stations wherein duty-free shops are established;

3/ Beneficiaries described under the provisions of Paragraph (d) and (e) of Sub Article (1) of this Article may purchase duty free goods from duty free shops established in Addis Ababa and other places wherein duty free shops are established by the special permission of the Commission;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (3) of this Article, any incoming passenger may purchase duty free goods only before crossing customs check point;

5/ For the purpose of this Article any staff of an airline or railway transport company who is travelling as member of the airline or railway crew shall not be considered as passenger when returning back to Ethiopia from their trip.

**፵፮. <u>የቀረጥ ነፃ ዕቃ ተጠቃሚ ባለመብቶች ሊያሟሉ የሚገባቸው ማስረጃዎች</u>**

የቀረጥ ነፃ ዕቃ ተጠቃሚዎች ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ መግዛት ሲፈልጉ:-

፩/ ገቢ ወይም ወጪ መንገደኞች ፓስፖርታቸውን ወይም ሌላ የጉዞ ሰነድ ለቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

፪/ ልዩ የቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚዎች የመጠቀሚያ ደብተር ከፓስፖርታቸው ወይም መታወቂያቸው ጋር እንዲሁም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ እንደሁኔታው ለቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ማቅረብ አለባቸው።

**፵፯. <u>የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት ግዴታዎች</u>**

ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን ፈቃድ ያገኘ ሰው፡-

፩/ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዘሩ በቀረጥ ነፃ መደብር ውስጥ የሚሸጡ ዕቃዎች "ከቀረጥ ነፃ" የሚል የማይጠፋ ምልክት ያለባቸው ሆነው ወደ ሀገር እንዲገቡ ያደርጋል፤

፪/ ኮሚሽኑን በማስፈቀድ በዚህ ደንብ የተመለከቱ መረጃዎችን የሚይዙ የሽያጭ ደረሰኞችን የዕቃዎች ገቢና ወጪ ቫውቸሮችን እንዲሁም የመከታተያ ሌጀሮችን ያሳትማል፤

፫/ በውጭ ምንዛሬ ግብይት ለመፈጸም ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

**46. <u>Evidences to be Submitted by Beneficiaries of Duty Free Goods</u>**

Beneficiaries of duty free goods shall submit the following documents to the duty free shops, when they want to purchase duty free goods:

1/ Incoming and outgoing passengers shall submit their passport or other travelling documents;

2/ The special beneficiaries of duty-free privileges shall submit coupon together with their passport or identification card, and supporting letter from the Ministry of Foreign Affairs, as the case may be.

**47. <u>Duties of Duty Free Shop Licensee</u>**

Any duty free shop and store owner shall:

1/ Ensure that goods listed under the Directive to be issued by the Minister of Finance are imported with a non-erasable mark of "duty free";

2/ With the permission of the Commission, have sales receipts, goods receiving and delivery vouchers, and ledger books issued containing the necessary data and information described under this Regulation;

3/ Obtain a permit from the National Bank of Ethiopia to sell goods with foreign currency;

Hima _ Tax Solutions Firm

፬/ ማንኛውም ወደ ተፈቀደው ቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብርም ሆነ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን የሚገባ ወይም የሚወጣ ዕቃ በቅድሚያ በኮሚሽኑ የተፈቀደ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

፭/ የቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን በዚህ ደንብ ለተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ብቻ መሸጥ እና ገገርዎች መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

፮/ በቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች ሽያጭ በደረሰኝ ማከናወን አለበት፤

፯/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም አለበት፤

፰/ ወርሃዊ የሽያጭ እና የክምችት ሪፖርት ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፤

፱/ የግብይት መረጃውን በአግባቡ በሕጋዊ የመዝገብ አያያዝ ስርዓት መዝግቦ መያዝና በየጊዜው ወቅታዊ ማድረግ አለበት፤

፲/ የቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን ክምችትና ሽያጭ ለመቆጣጠር የሚያስችል በአውቶሚሽን የተደገፈ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፤

፲፩/ ኮሚሽኑ ለሚመድባቸው የጉምሩክ ተቆጣጣሪዎች ቢሮና የቢሮ ቁሳቁስ ማሟላት እና ሰነዶችንና አስፈላጊ መረጃዎችን ማቅረብ አለበት፤

፲፪/ ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርቱን በውጭ ኦዲተር በማስመርመር የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፤

፲፫/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር የሽያጭ ሠራተኞችን በአግባቡ ለማስተዳደር የሥራ የዲሲፕሊን መመሪያ ሊኖረው ይገባል፤

4/ Ensure that any goods entered into or withdrawn from the permitted duty free shop or duty free store are approved in advance by the Commission;

5/ Sell duty free goods only to the beneficiaries mentioned under this Regulation and ensure that they have evidence showing that they are beneficiaries;

6/ Issue invoices for every sales transaction;

7/ Use cash register machines;

8/ Submit his monthly sales and stock report to the Commission;

9/ Duly record and update his records of sales transactions with a system of books of account;

10/ Establish modern automation system to control the stock and sales of duty free goods;

11/ Arrange office with full facilities and materials and submit necessary documents and evidences to the customs inspectors assigned by the Commission;

12/ Submit annual financial reports audited by external auditor within three months after the end of the budget year;

13/ Issue and implement Directives of disciplinary measures to properly administer employees working as vendors in the duty free shop;

Hima – Tax Solutions Firm

፲፬/ በተሰጠው ፈቃድ ተጨማሪ ሱቅ ለመክፈት ሲፈልግ በቅድሚያ ለኮሚሽኑ በማሳወቅ የሥራ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፲፭/ በተፈቀደው የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብርም ሆነ የቀረጥ ነፃ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ላይ መሠረታዊ ለውጥ ከማድረጉ በፊት ለኮሚሽኑ በማሳወቅ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፲፮/ በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ወይም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን ላይ ተፈፃሚነት ያላቸውን የጉምሩክ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና አሠራሮች ማክበር አለበት፤

፲፯/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብርን ፈቃዱን በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የለበትም፤

፲፰/ ለሀገር ውስጥ መንገደኞች ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ዕቃ መሸጥ የለበትም፤

፲፱/ በመመሪያ ከሚወሰነው መጠን በላይ ለተጠቃሚዎች ዕቃ መሸጥ የለበትም፤

፳/ በጉዞ ስረዛ ምክንያት በመንገደኞች የተገዛ ዕቃ ተመላሽ የተደረገ እንደሆነ ሽያጩ ተሰርዞ በዕቃው ላይ በውጭ ምንዛሪ የተከፈለውን ገንዘብ ለመንገደኛው ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

**፵፰. የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘንን ስለመቆጣጠር**

ኮሚሽኑ፡-

፩/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፤

14/ Notify the Commission and obtain permission to open additional duty free shop when he requires to do so;

15/ Shall notify the Commission and obtain permission there from to make any material change on the duty free shop or the duty free store;

16/ Comply with customs laws, Regulations, Directives, and Procedures applicable on duty free shops and duty free stores;

17/ Not transfer his duty free shop license and permit to any other person;

18/ Not sale goods from duty free shop to domestic passengers;

19/ Not sale goods to the customers above the limit determined by Directives;

20/ Cancel the sale and refund the foreign currency paid for the goods purchased by the outgoing passengers where the goods are returned to the duty free shop due to cancellation of the trip.

**48. Control of Duty Free Shops and Duty Free Stores**

The Commission shall:

1/ Notify the National Bank of Ethiopia of persons granted with permission for duty free shop and duty free stores;

፪/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብርን እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘንን የሽያጭ አፈፃፀም ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫/ በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እና በቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን ውስጥ የተከማቹ ዕቃዎችን ድንገተኛ ቁጥጥር እና ኦዲት ያደርጋል፤

፬/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮች ለቀረጥ ነፃ ባለመብቶች ብቻ አገልግሎት መስጠታቸውን ይቆጣጠራል፤

፭/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር እና የቀረጥ ነፃ ዕቃ መጋዘን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ተጨማሪ መደብር ወይም መጋዘን ለማቋቋም የሚያቀርበውን ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር አሠራር

### ፵፱. ለተጠቃሚዎች መረጃ የመስጠት ኃላፊነት

፩/ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት ከመደብሩ የቀረጥ ነፃ ዕቃ ለመግዛት መብት ያላቸው ሰዎች መብት እና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ማድረግ አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው መረጃ በሱቁ ውስጥ የሚሸጡ ዕቃዎችን ዝርዝር እና የተጠቃሚዎችን መብትና ግዴታ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

2/ Establish and implement modern data and record management system which enables it control and follow up sales activities and stocks of duty free shops and duty free stores;

3/ Conduct surprise inspections and audit on duty free shops and duty free stores;

4/ Ensure that duty free shops are providing service only to the beneficiaries;

5/ Decide on applications lodged for the establishment of extra duty free shops and stores.

## CHAPTER FOUR

## OPERATIONS OF DUTY FREE SHOPS

### 49. Responsibility to Provide Information to Customers

1/ Any duty free shop owner shall provide information on their rights and duties to persons who have the right to purchase goods from the duty free shop;

2/ The information to be provided under this Article shall include displaying lists of goods sold in the duty free shop and rights and duties of the beneficiaries.

Hima _ Tax Solutions Firm

Hima _ Tax Solutions Firm

## ፶. በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ውስጥ የዕቃዎች አያያዝ

፩/ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት:-

ሀ) ለምግብነት የማይውሉ ዕቃዎችን ለእይታ አመቻችቶ ማስቀመጥ፤

ለ) ለምግብነት የማይውሉ ዕቃዎችን ተጠቃሚዎች ተስማሚነታቸውን እንዲሞክሩ መፍቀድ፤

ሐ) ለተጠቃሚዎች ሽያጭ ማከናወን፤

፪/ ዕቃዎች ከመሸጣቸው በፊት ለእይታ ወይም ለሙከራ ወይም ለሌላ ማንኛውም ምክንያት ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ውጪ እንዲወሰዱ አይፈቀድም፡፡

## ፶፩. በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ውስጥ የሚሸጡ ዕቃዎችና የሽያጩ አፈፃፀም

፩/ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት በመደብሩ ውስጥ መሸጥ የሚችለው የሚከተሉትን ዕቃዎች ነው:-

ሀ) ማንኛውንም ዓይነት የአልኮል መጠጥ፤

ለ) ታሽገው የሚሸጡ ምግቦችና ለስላሳ መጠጦች፤

ሐ) የተዘጋጁ አልባሳትና ጫማ፤

መ) የባህልና የኪነ-ጥበብ ዕቃዎች፤

ሠ) የግብርናና የኢንዱስትሪ ውጤቶች፤

ረ) ትምባሆ፣ ሲጋራና ሲጋር፤

ሰ) ጌጣጌጦችና የመዋቢያ ዕቃዎች፤

ሸ) ሽቶዎችና ቅባቶች፤

## 50. Handling of Goods in Duty Free Shop

1/ Any owner of a duty free shop shall perform the following activities in his duty free shop:-

a) displaying non-consumable goods;

b) allowing customers to check the fitness of non-consumable goods;

c) performing sales activities to customers;

2/ Goods may not be removed from the duty free shop for checking or displaying or for any other reasons before sale.

## 51. Goods Sold in Duty Free Shops and Performance of the Sale

1/ Duty Free Shop owner may sale the following goods in duty free shops:-

a) alcohol drinks of any type;

b) packed foods and soft drinks;

c) ready-made clothes and shoes;

d) cultural and artistic goods;

e) agricultural and industrial products;

f) Tobacco, cigarette and cigar;

g) ornaments and beauty make up goods;

h) perfumes and cosmetics products;

ቀ) ኤሌክትሮኒክስና አክሰሰሪዎች፤

በ) የቤትና የግል መገልገያ ዕቃዎች፤እና

ተ) ሌሎች በገንዘብ ሚኒስቴር የሚፈቀዱ ዕቃዎች፡፡

፪/ በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ውስጥ የሚሸጥ ማንኛውም ዕቃ መሸጥ ያለበት በውጭ ምንዛሪ ብቻ ነው፤

፫/ የገንዘብ ሚኒስቴር የቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚዎች ከቀረጥ ነፃ ሱቆች በአንድ ጊዜ መግዛት የሚችሉትን የዕቃ መጠን በመመሪያ ይወስናል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት ከቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብሮች በአንድ ጊዜ መግዛት የሚችሉት የዕቃ መጠን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይወሰናል፡፡

**፶፪. የሪከርድና የሪፖርት ሥርዓት**

፩/ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን፣ የተሸጠውን እና ከመጋዘን ውስጥ የቀረውን ዕቃ በየጊዜው የሚመዘግብበት የሪከርድ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፤

፪/ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት የሚጠቀመው የዕቃ ክምችት አስተዳደር ሥርዓት የዕቃዎቹን አገባብ ቅደም ተከተል የሚከተል መሆን አለበት፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የዕቃዎች ዓይነት፣ ብዛት፣ ግብይትና የዕቃ ክምችት እንቅስቃሴ የሚመዘግብበት የንግድ መዝገብ ሊኖረው ይገባል፤

i) electronics and accessories;

J) household goods and personal effects; and

k) other goods that are allowed by the Ministry of Finance.

2/ Any goods in duty free shops shall be sold in foreign currency;

3/ The quantity of goods to be sold at one transaction to beneficiaries of duty free shops shall be determined by Directives to be issued by the Ministry of Finance;

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of this Article the quantity of goods to be sold at one transaction to diplomatic communities shall be determined by the Ministry of Foreign Affairs.

**52. Recording and Reporting System**

1/ Any owner of duty free shop shall have a system of record for regularly registering goods imported, sold and unsold stock in the warehouse;

2/ Any owner of duty free shop shall use a system of stock management that follows first in first out method;

3/ Without prejudice to the Provisions of Sub-Article (1) of this Article any owner of duty free shop shall have commercial record management system supported by modern information technology for registering the types, quantities, transaction of goods and the movement of stocks;

Hima _ Tax Solutions Firm

፬/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት በየወሩ ከሚያቀርበው የሽያጭ እና የዕቃ ክምችት ሪፖርት በተጨማሪ በዓመቱ መጨረሻ የተጠቃለለ የሒሣብና የንግድ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፶፫. <u>የቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን ስለማስተላለፍ እና ስለማስወገድ</u>

፩/ በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ፈቃዱ የተሰረዘበት ማንኛውም የቀረጥ ነፃ መደብር ባለቤት ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎችን ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ማስተላለፍ ይችላል፤

፪/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት የራሱ ጥፋት ባልሆነ ምክንያት የተበላሹ፣ የተጎዱ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ገበያ ላይ የማይውሉ ዕቃዎችን ለይቶ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፤

፫/ በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ውስጥ የሚገኙ ቀረጥ እና ታክስ ያልተከፈለባቸው የተበላሹ፣ የተጎዱ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ገበያ ላይ የማይውሉ ዕቃዎች የማስወገጃ ወጪው በድርጅቱ ባለቤት እንዲሸፈን ሆኖ በኮሚሽኑ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

፶፬. <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ስለመጠቀም</u>

፩/ ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት ለእያንዳንዱ ግብይት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡ መሣሪያው አገልግሎት መስጠት በማይችልበት ጊዜ ለእያንዳንዱ ግብይት በኮሚሽኑ ፈቃድ የታተመ ደረሰኝ መስጠት ይኖርበታል፤



4/ The owner of the duty free shop, in addition to monthly transaction and stock report, shall submit a consolidated annual financial and business transaction report to the Commission.

53. <u>Transfer and Disposal of Duty Free Goods</u>

1/ A person whose permit is revoked in accordance with the provisions of this Regulation may transfer goods imported duty free to a person who has similar privileges;

2/ The owner of a duty free shop shall report to the Commission goods that are spoiled or damaged or goods that cannot be sold for reasons not attributable to his fault;

3/ Goods in the duty free shop that are spoiled or damaged, or that cannot be sold for any reason and on which customs duty and tax is not paid shall be disposed by the Commission at the cost of the company owner.

54. <u>Use of Sales Register Machine</u>

1/ Any duty free shop owner shall have the duty to use sales register machine. In situations where the sales register machine is out of order shall issue invoices printed on permission from the Commission;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ የቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለሚፈጽመው ጥፋት በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተደነገገው ቅጣት እንደሁኔታው ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

## ፶፭. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፡-

፩/ ለቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር ባለቤት በውጭ ምንዛሪ ግብይት መፈፀም የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፤

፪/ በቀረጥ ነፃ ዕቃ መሸጫ መደብር በውጭ ምንዛሪ የሚደረገውን ግብይት ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የቀረጥ ነፃ መደብር ባለቤቶች ከሽያጭ ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በወቅቱ ገቢ ማድረጋቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

## ፶፮. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡-

፩/ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የቀረጥ ነፃ መብት ተጠቃሚ የሆኑ የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላትን በመለየት ይመዘግባል፤

፪/ የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸውን የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላትን ዝርዝር ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤

፫/ የቀረጥ ነፃ መብት ላላቸው የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት የኮታ መጠን በመወሰን የመጠቀሚያ ደብተር ይሰጣል፤

2/ The Tax Administration Proclamation shall be applicable as may be necessary on any fault committed by the owner of duty free shop in connection with the use of sales register machine.

## 55. Duties and Responsibilities of the National Bank of Ethiopia

The National Bank of Ethiopia shall:

1/ Provide a permit to the duty free shop owner for transacting in foreign currency;

2/ Establish and implement a system which enables it control the transactions of duty free shops performed in foreign currency and follow-up the timely deposit of foreign currency returns to banks.

## 56. Duties and Responsibilities of the Ministry of Foreign Affairs

The Ministry of Foreign Affairs shall:

1/ Identify and register the diplomatic community with duty privileges based on international agreements and conventions;

2/ Notify the Commission of members of diplomatic community having duty free privileges;

3/ Provide coupon cards to and determine quota of members of diplomatic community who have duty free privileges;

Hima _ Tax Solutions Firm

፬/ የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት ተልኳቸውን አጠናቀው ከሀገር ሲወጡ የመጠቀሚያ ደብተራቸውን በመረከብ ይህንኑ ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፯. ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ስለማድረግ

፩. የገንዘብ ሚኒስቴር በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በአስተዳደራዊ ምክንያቶች በአዋጁ አንቀጽ ፩፻፳፱ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዕቃዎች በመመሪያ ወይም በሚያስተላለፈው ውሳኔ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደሀገር እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል፤

፪. የጉምሩክ ኮሚሽን በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር በገቡ ዕቃዎች ሊከፈል ይገባ የነበረውን ቀረጥ እና ታክስ በመመዝገብ ዕቃዎቹ እንዲገቡ ያደርጋል፤ የተመዘገበውን ቀረጥ እና ታክስ መጠን በየሦስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያስታውቃል፤

፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ሆነው ወደሀገር በገቡ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን ቀረጥ እና ታክስ እንዲሁም የተፈቀደበትን ምክንያት የሚያሳይ የተጠቃለለ መረጃ በዓመታዊ የመንግሥት ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፡፡

4/ Collect coupon cards from members of the diplomatic community who leave the country accomplishing their mission and notify same to the Commission.

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 57. Exemption from Taxes and Duties

1/ The Ministry of Finance may for economic, social or administrative reasons exempt goods imported into the country from taxes and duties by Directive or through a decision to be rendered in accordance with the power vested in it under Sub-Article(1) of Article 129 of the Proclamation;

2/ The Customs Commission shall register the taxes and duties forgone on goods imported free of taxes and duties pursuant to Sub-Article (1) of this Article, allow the goods to enter into the country and submit quarterly reports to the Ministry on the amount of taxes and duties registered as forgone;

3/ The Ministry of Finance shall incorporate consolidated statement in the annual public accounts showing the amount of taxes and duties forgone and the reasons for the exemption.

Hima _ Tax Solutions Firm

**፶፰. መመሪያ ስለማውጣት**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፶፱. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የወል ጊዜያዊ የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ አግኝተው ሲሠሩ የነበሩ ሰዎች ወይም ድርጅቶች በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ ሌሎች የመጋዘን አይነቶች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ ደንብ ክፍል አራት እና ደንቡን መሠረት በማድረግ በሚወጣ መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሥራ ላይ ባለው መስፈርት መሠረት ፈቃዳቸው እንዲታደስ ይደረጋል፤

፪/ ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች ሥራ ላይ በነበረው ደንብ መሠረት ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

**፷. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ደንቦች**

፩/ የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡-

ሀ) የጉምሩክ መጋዘን ሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፬/፲፱፻፺፣

ለ) የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፰ /፲፱፻፺፮፣

**58. Issuance of Directives**

The Ministry may issue Directives for the proper administration of this Regulation.

**59. Transitory Provisions**

1/ Persons and organizations who have been operating Temporary Public Customs Warehouses with a license obtained from the Commission shall fulfil the requirements under Chapter four of this Regulation within two years and other types of warehouses within one year from the date of issuance of this Regulation. Hence, until the period granted herein, their license shall be renewed upon fulfilling the requirements under the repealed Regulation;

2/ Cases pending before the effective date of this Regulation shall be disposed in accordance with the repealed Regulation.

**60. Inapplicable and Repealed Regulations**

1/ The following Regulations are hereby repealed by this Regulation:

a) Customs Warehouse License Issuance Council of Ministers Regulation No. 24/1997;

b) Customs Clearing Agents Council of Ministers Regulation No.108/2004;

Hima _ Tax Solutions Firm

፪/ ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ይህ ደንብ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፷፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

2/ Any Regulation or Directive inconsistent with this Regulation shall have no effect on matters covered under this Regulation.

**61. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force upon the Date of approval by the Council of Ministers on the 21st day of May, 2022.

**Done at Addis Ababa, on this 5th Day of July, 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Hima _ Tax Solutions Firm

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት